# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ይህ እውነታ፡ ቀደም ብሎ፡ በነቢያት ትንቢት፥ ኋላም፡ በሐዋርያት ስብከት ከተላለፈው መለኮታዊ መልእክት ጋር፡ ራሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"መልካም ያደረጉ፡ ለሕይወት ትንሣኤ፡ ክፉ ያደረጉም፡ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉ!"* ሲል በተናገረው ቃሉ አረጋግጦታል።

*"'ትንሣኤ ሙታን የለም!' የሚሉ ሰዱቃውያን፡ ሊፈትኑት፡ '...መምህር ሆይ! ሙሴ፡ "አንድ ሰው፡ ልጅ ሳይወልድ ቢሞት፡ ወንድሙ፡ ሚስቱን አግብቶ፡ ለወንድሙ ዘር ይተካ!" አለ። ሰባት ወንድማማች፡ አንዲት ሴትን* በተራ አግብተዋት፡ ሰባቱም፡ ከእርሷ ሳይወልዱ፡ *ከኹሉ በኋላ ሴቲቱ ሞተች። ኹሉም አግብተዋታልና፡ በትንሣኤ ቀን፡ ከሰባቱ፡ ለማናቸው ሚስት ትኾናለች?'"* ብለው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በጠየቁት ጊዜ፡ *"ቅዱሳት መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና፡ ትስታላችሁ። በትንሣኤስ፡ እንደእግዚአብሔር መላእክት፡ በሰማይ ይኾናሉ እንጂ፡* እንደሥጋውያንና ምድራውያን ሰዎች፡ *አያገቡም፤ አይጋቡምም። ስለትንሣኤ ሙታን ግን፡ 'እኔ፡ የአብርሃም አምላክ፥ የይስሐቅም አምላክ፥ የያዕቆብም አምላክ ነኝ!' የሚል፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ፡ ወደእናንተ የተባለውን አላነበባችሁምን?* እግዚአብሔር፡ *የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ፡ የሙታን አምላክ አይደለም!"* ብሎ በሰጣቸው መልስ፡ የሙታን ትንሣኤ መኖሩንና ከትንሣኤ በኋላ ያለው ሕይወት፡ የእነማንን እንደሚመስል ገልጧል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከመጨረሻ ምጽአቱ ጋር በሚከሠተው የሙታን ትንሣኤ፡ የሰው ልጆች ዕድል ፈንታ፡ ምን ዓይነት እንደሚኾን፡ ያም ትንሣኤ፡ እንዴት እንደሚካኼድ፡ መልካም ዘርን በዘራ ገበሬና ክፉ ዘርን በዘራ ጠላት፡ በእርሻና በዘር፡ በስንዴና በእንክርዳድ፡ በአጫጆችና በመከር እየመሰለ ባስተማራቸው ትምህርቶች አስረድቷል።

*"ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ!"* ያለው ጌታ፡ እነዚህን የምሳሌ ትምህርቶቹን ሲተረጉም፡ *"መልካምን ዘር የዘራው፡ የሰው ልጅ* [ኢየሱስ ክርስቶስ] *ነው፡ እርሻውም፡ ዓለም ነው፡ መልካሙም ዘር፡ የመንግሥት* [የእግዚአብሔር] *ልጆች ናቸው፥ እንክርዳዱም፡ የክፉው* [የዲያብሎስ] *ልጆች ናቸው፡* [ክፉውን ዘር] *የዘራውም ጠላት፡ ዲያብሎስ ነው፥ መከሩም፡ የዓለም መጨረሻ ነው፡ አጫጆችም፡ መላእክት ናቸው። እንግዴህ፡ እንክርዳድ ተለቅሞ፡ በእሳት እንደሚቃጠል፡ በዓለም መጨረሻ፡ እንዲሁ ይኾናል።"* አለ። ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ይህንኛውን ትርጓሜውን የጨረሰው፡ እናንተና እኔ፥ እኛንም የመሰሉት ኹሉ፡ ልብ ብለን እንድናስተውለው በሚፈልገው፡ *"የሚሰማ ጆሮ ያለው፡ ይስማ!"* በሚለው የማስጠንቀቂያ ቃሉ ስለኾነ፡ ይህ መለኮታዊ ቃል፡ የዘወትር ማንቂያ ደወል ሊኾነን ይገባል።

ይህ ትርጓሜው፡ ጌታችን፡ ስለዳግም ምጽአቱ፡ ለደቀ መዛሙርቱ ካመለከታቸው፡ እንዲህ ከሚለው ቃሉ ጋር ይስማማል፦ *"ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ፡ ወዲያው ፀሓይ ይጨልማል፤ ጨረቃም፡ ብርሃኗን አትሰጥም፡ ከዋክብትም፡ ከሰማይ ይወድቃሉ፤ የሰማያት ኃይላትም ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም፡ የሰው ልጅ ምልክት፡ በሰማይ ይታያል።*

## ምዕራፍ ፫፡ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
### ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን።
### ስለትንሣኤ ዘጉባዔ።

---

*"በዚያን ጊዜም፡ የምድር ወገኖች ኹሉ፡ "ዋይ! ዋይ!" ይላሉ፤ የሰው ልጅንም፡ በኃይልና በብዙ ክብር፡ በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል። መላእክቱንም፡ ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፤ ከሰማያትም ዳርቻ [፳፬] እስከዳርቻው፡ ከአራቱ ነፋሳት፡ ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ።"*

*ጥያቄ፡- ይህ፡ የትንሣኤ ሙታን ትምህርትህ፡ አሁንም፡ ምሥጢርነቱ፡ ገና እንደረቀቀብን ነው፤ ለመኾኑ፡ የሙታን ትንሣኤ፡ እንዴት ሊኾን ይችላል? ማለትም፡ በመቃብር ጉድጓድ ውስጥ ተጥሎና አፈር ኾኖ በስብሶ መቅረትን፡ ከእኛ በፊት በሞቱት እያየንና እየረጋገጥን፡ እንደገና፡ ሕያው ኾኖ፡ በአዲስ አካል መነሣት፡ "ይቻላል!" ብሎ ማመን፡ ለእኛ ብጤ፡ በእርግጥ ይከብዳል፤ አንተስ አይመስልህም?*

**መልስ፡-** እንደቀሩት ምሥጢራት ኹሉ፡ አዎን! ይህም፡ የትንሣኤ ምሥጢር፡ ሊረቅቅባችሁና ሊከብድባችሁ ይችላል። ነገር ግን፡ ይህን ምሥጢር፡ እንደሌሎቹ ምሥጢራት ኹሉ፡ ልትረረዱት፡ አውቃችሁ በሃይማኖት ልትቀበሉትም የምትችሉት፡ በመንፈሳዊው አእምሮአችሁ ኾኖ፡ ከዚያ ጋር ደግሞ፡ "ለእግዚአብሔር፡ የሚሳነው ነገር የለም!" የሚለውን መልአካዊ ቃል፡ በሃይማኖታዊ ምግባር ላይ ስታውሉት መኾኑን፡ ባለፈው ውይይታችን ጊዜ፡ ቀደም አድርጌ አቅርቤላችሁ ከነበረውና በየልቦናችሁ ከተመዘገበው ሐተታ፡ ልታስታውሱት ትችላላችሁ።

ይህን የረቀቀ ምሥጢር፡ በቀላሉ አውቃችሁና ተረድታችሁ፡ ለማመን ትችሉ ዘንድ፡ "እንቅልፍ" ስለሚባለው ትንግርት፡ እስኪ፡ ለጥቂት አፍታ፡ ጠለቅ ብለን ለመመራመር እንሞክር! አብሮን የሚኖር ኹነታ ስለኾነና ስለተላመድነው፡ እኛ ሰዎች፡ "እንቅልፍ፡ን"፡ እንደተራ ነገር እንቈጥረዋለን እንጂ፡ "ምን ምሥጢር ነው?" ብለን፡ ከቍም ነገር አስገብተንና ጊዜ ሰጥተን፡ ልናጤነው እንኳ አንፈልግም።

የቀደሙት አባቶቻችንና እናቶቻችን ግን፡ እንቅልፍን፡ "የሞት ታናሽ ወንድም" እያሉ፡ በከፍተኛ ግምት ያውቁት እንደነበረ፡ ከልጅ ልጅ በተላለፈልን ትውፊት ተረድተናል። አዎን! እናንተም፥ እኔም፡ በዚህ "እንቅልፍ"፡ በየቀኑ ምሽት፡ ከጨለማው ጋር ተወስደንና እንደሞተ ሰው በድን ኾነን ካደርን በኋላ፡ በየማለዳው ደግሞ፡ ከፀሓይ ብርሃን ጋር፡ ባንነን፡ ወይም፡ አውቀን፡ ወይም፡ በአንዳች ነገር ተቀስቅሰን እንነቃና እንነሣለን። ታዲያ! ፈጣሪያችን፡ በዚህ፡ በ"እንቅልፍ" አማካይነት፡ ከሌሎቹ ምክንያቶቹ ጋር፡ በየዕለቱ፡ ምን ትንግርትን እያሳየንና እያስተማረን ይመስለናል? እንዲሁም፡ አዝርዕትና አትክልት፥ ዕጽዋትና ሌሎቹም ተንቀሳቃሽ ፍጥረታት፡ "ጠፉ! ደረቁ!" ከተባሉ በኋላ፡ እንደገና ብቅ ብቅ እንዲሉና እንሠራርተው እንዲነሡ፥ እንዲያቈጠቍጡም በሚያደርግባቸው፡ በበጋውና በክረምቱ፥ በበልጉና በአበባው ወራት አማካይነት፡ ከቶ ምንድር "ምሥጢር"ን እየገለጸልን ይኾን? እኛን ስለሚመለከተው፡ ስለትንሣኤ ሙታን አይደለምን? አዎን! ነው እኮ!

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

በዚህ ረገድ፡ አምላካችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰዎች የዕለት የግብርና ሥራ ውስጥ ገዝፎ የሚታየውን እርሻን፡ ምሳሌ አድርጎ፡ ስለትንሣኤ ሙታን ነገር፡ በአጭር ቃል የገለጸውን፡ ልጥቀስላችሁ! *"እውነት፡ እውነት እላችኋለሁ! የስንዴ ቅንጣት፡ በምድር ወድቃ ካልሞተች፡ ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን፡ ብዙ ፍሬን ታፈራለች።"* ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም፡ ይህን መለኮታዊ ቃል መሠረት በማድረግ፡ እንዲህ ሲል በጻፈው መልእክቱ፡ የሙታንን ትንሣኤ ምሥጢር፡ እንዴት አድርጎ፡ አግዝፎና አጉልቶ እንዳስረዳ አስተውሉት፦

*"'ሙታን እንዴት ይነሣሉ? በምንስ ዓይነት አካል ይመጣሉ?' የሚል ሰው ይኖር ይኾናል። አንተ ሞኝ! አንተ የምትዘራው ካልሞተ፡ ሕያው አይኾንም፤ የምትዘራውም፡ ስንዴ ቢኾን÷ ከሌላም ዓይነት፡ የአንዱ ቢኾን፡ ቅንጣት ብቻ ነው እንጂ፡ የምትዘራው፡ የሚኾነውን አካል አይደለም። እግዚአብሔር ግን፡ እንደወደደ፡ አካልን ይሰጠዋል፤ ከዘሮችም፡ ለእያንዳንዱ፡ የገዛ አካሉን ይሰጠዋል። ሥጋ ኹሉ፡ አንድ አይደለም፤ የሰው ሥጋ ግን፡ አንድ ነው፤ የእንስሳም ሥጋ ሌላ ነው፤ የወፎችም ሥጋ ሌላ ነው፤ የዓሣም ሥጋ ሌላ ነው። ደግሞ፡ ሰማያዊ አካል አለ፤ ምድራዊም አካል አለ፤ ነገር ግን፡ የሰማያዊ አካል ክብር፡ ልዩ ነው፤ የምድራዊም አካል ክብር፡ ልዩ ነው። የፀሐይ ክብር፡ አንድ ነው፤ የጨረቃም ክብር፡ ሌላ ነው፤ የከዋክብትም ክብር፡ ሌላ ነው፤ በክብር፡ አንዱ ኮከብ፡ ከሌላው ኮከብ ይለያልና።*

*"የሙታን ትንሣኤ ደግሞ፡ እንዲሁ ነው። በመበስበስ ይዘራል÷ ባለመበስበስ ይነሣል፤ በውርደት ይዘራል÷ በክብር ይነሣል፤ በድካም ይዘራል÷ በኃይል ይነሣል፤ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል÷ መንፈሳዊ አካል ይነሣል። ፍጥረታዊ አካል ካለ፡ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ። እንዲሁ ደግሞ፡ 'ፊተኛው ሰው አዳም፡ ሕያው ነፍስ ያለው ኾነ!' ተብሎ ተጽፏል፤ ኋለኛው አዳም* [ኢየሱስ ክርስቶስ] *ሕይወትን የሚሰጥ፡ መንፈስ ኾነ! ነገር ግን፡ አስቀድሞ፡ ፍጥረታዊው÷ ቀጥሎም፡ መንፈሳዊው ነው እንጂ፡ መንፈሳዊው፡ መጀመሪያ አይደለም።*

*"የፊተኛው ሰው፡* [አዳም] *ከመሬት ስለኾነ፡ መሬታዊ ነው፤ ኹለተኛው ሰው፡* [ኢየሱስ ክርስቶስ]*፡ ከሰማይ ነው። መሬታዊው፡ መሬታዊ እንደኾነ፡ መሬታውያን የኾኑት ደግሞ፡ እንዲሁ፡ መሬታውያን ናቸው፤ ሰማያዊው፡ ሰማያዊ እንደኾነ፡ ሰማያውያን የኾኑት ደግሞ፡ እንዲሁ፡ ሰማያውያን ናቸው። የዚያንም፡ የመሬታዊዉን መልክ እንደለበስን፡ የሰማያዊዉን መልክ ደግሞ፡ እንለብሳለን።"* ፶፪

በዚህ መሠረት፡ ሙታን፡ በትንሣኤ፡ ወንዶች፡ በአቅመ አዳም፡ የ፴ ዓመት ጕልማሳ፤ ሴቶች፡ በአቅመ ሔዋን፡ የ፲፭ ዓመት ቆንጆ ኾነው ይነሣሉ፤ ሲነሡም፡ ስንኳንስ ታላላቅ ኾነው የሞቱት፡ በእናታቸው ማሕፀን ተፀንሰው፡ ደም ኾነው የወረዱት እንኳ አይቀሩም፤ በመካከላቸውም፡ አጭር፡ ረዥም÷ ቀይ፡ ጥቁር÷ ጎባጣ፡ መላጣ÷ ዕውር፡ አንካሳ አይኖርም።

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::

## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን::

### ስለትንሣኤ ዘጉባዔ::

---

ይኹን እንጂ: ጻድቃን: ብርሃን ለብሰውና ብርሃን ተጎናጽፈው÷ ከፀሓይ ሰባት እጅ አብርተውና ፈጣሪያቸው ኢየሱስ ክርስቶስን መስለው ሲነሡ: ኃጥአን ግን: ሲነሡ: ጨለማን ለብሰውና ጨለማን ተጎናጽፈው÷ ከቁራ ሰባት እጅ ጠቁረውና አለቃቸውን ዲያብሎስን መስለው ነው::

### ስለፊተኛውና ስለኋለኛው ትንሣኤ::

ጥያቄ:- *የሥጋን ሞት ሳይሞቱ: ማለትም: በዚህ ዓለም: በሕይወተ ሥጋ ኢያሉ: የሚኾነው ትንሣኤ: እንዴት ነው? "ኹለት ዓይነት ትንሣኤ አለ!" የሚባለውስ: እንደምንድር ነው?*

መልስ:- አዎን! ትንሣኤ: ኹለት ነው፤ "ፊተኛውና ኋለኛው"÷ ወይም: "አንደኛውና ኹለተኛው"÷ ወይም: "መጀመሪያውና መጨረሻው"÷ ወይም: "ትንሣኤ ዘመንፈስና ትንሣኤ ዘጉባኤ" ይባላል:: ስለሙታን ትንሣኤ: ቀደም ብዬ ከጠቀስሁላችሁ: ከመለኮታዊው አዋጅ ጋር: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: በሌላ ጊዜና ኹኔታ: አበክሮ: ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረውን ደግሞ በማስተዋል ተመልከቱት! ይህም: *"እውነት: እውነት እላችኋለሁ! ቃሌን የሚሰማ÷ የላከኝንም የሚያምን: የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ ከሞትም ወደሕይወት ተሻገረ እንጂ: ወደፍርድ አይመጣም:: እውነት እውነት እላችኋለሁ! ሙታን: የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ እርሱም: አኹን ነው፤ የሚሰሙትም: በሕይወት ይኖራሉ:: የእግዚአብሔር ልጅ: የሰው ልጅ ነውና...በመቃብር ያሉቱ ኹሉ: ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል!"* የሚለው ቃሉ ነው::

በዚያ አዋጅ ላይ የተመሠረተው: የሐዋርያው ቃል: የሙታን ትንሣኤን ነገር: እንዲህ እያለ: አስፋፍቶ ይገልጸዋል:- *"እነሆ: አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፤ ኹላችን አናንቀላፋም፤ ነገር ግን: የኋለኛው መለከት ሲነፋ: ኹላችን: በድንገት: በቅጽበተ ዓይን እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና፤ ሙታንም: የማይበሰብሱ ኾነው ይነሣሉ፤ እኛም: እንለወጣለን::*

*"ይህ የሚበሰብሰው: የማይበሰብሰውን ሊለብስ÷ ይህም የሚሞተው: የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና:: ዳሩ ግን: ይህ የሚበሰብሰው: የማይበሰብሰውን ሲለብስ÷ ይህም የሚሞተው: የማይሞተውን ሲለብስ: በዚያን ጊዜ: "ሞት: ድል በመነሣት ተዋጠ!" ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል::"*

ሐዋርያው: በሌላ መልእክቱ: ይህን ምሥጢር: እንዲህ ሲል: በበለጠ ያብራራዋል:- *"ነገር ግን: ወንድሞች ሆይ! ተስፋ እንደሌላቸው: እንደሌሎች ደግሞ: እንዳታዝኑ: አንቀላፍተው ስላሉቱ:"* ማለትም: ቀደም ብለው: በሞተ ሥጋ ተለይተው ስለቆዩት: *"ታውቁ ዘንድ እንወድዳለን:: ኢየሱስ እንደሞተና እንደተነሣ ካመንን: እንዲሁ: በኢየሱስ ያንቀላፉቱን: እግዚአብሔር: ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና::*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

*"በጌታ ቃል የምንላችሁ፡ ይህ ነውና፤ እኛ፡ ሕያዋን ኾነን፡ ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር፡ ያንቀላፉቱን፡ አንቀድምም፤ ጌታ፡ ራሱ፡ በትእዛዝ÷ በመላእክትም አለቃ ድምፅ÷ በእግዚአብሔርም መለከት፡ ከሰማይ ይወርዳልና፤ በክርስቶስ የሞቱ፡ አስቀድመው ይነሣሉ፤ ከዚያም በኋላ፡ እኛ፡ ሕያዋን ኾነን የምንቀረው፡ ጌታን፡ በአየር ለመቀበል፡ ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም፡ ኹልጊዜ ከጌታ ጋር እንኾናለን፡፡ ስለዚህ፡ እርስ በርሳችሁ፡ በዚህ ቃል ተጽናኑ፡፡"* [፻፫]

ከዚህ ጋር ተያይዞ፡ ሊታይ የሚገባው፡ በራእየ ዮሐንስ ላይ የተጠቀሰው፡ የሺ ዓመቱ ምሥጢር ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በትንሣኤውና በዕርገቱ፡ የክፋትን÷ የኀጢአትንና የሞትን ኃይላት ድል ነሥቶ፡ መንፈስ ቅዱስ በዓለሙ ላይ እንዲወርድ በማድረጉ፡ የእግዚአብሔር ልጆች የተቀዳጁትን ድል የሚገልጸውን ይህንኑ ምሥጢር፡ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ፡ በራእዩ፡ አብራርቶ ጽፎት፡ እንዲህ ሲል ይነበባል፦ *"የጥልቁን መክፈቻና ታላቁን ሰንሰለት፡ በእጁ የያዘ መልአክ፡ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፡፡ የቀደመውንም እባብ÷ ዘንዶውን÷ እርሱም፡ ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው! ሺ ዓመትም አሠረው! ወደጥልቅም ጣለው! አሕዛብንም ወደፊት እንዳያስት፡ ሺ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ፡ በእርሱ ላይ ዘግቶ፡ ማኅተም አደረገበት! ከዚያም በኋላ፡ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል፡፡*

*"ከዚህ በኋላ፡ ዙፋኖች ተዘርግተው፡ የሰው ልጅ (ኢየሱስ ክርስቶስ) በላያቸው ተቀምጦ አየሁ! ስለኢየሱስ÷ ስለስሙና ስለእግዚአብሔር ቃል ሲሉ ስለተገደሉ ሰዎች ነፍሳትም፡ ቅን ፍርድን ፈረደላቸው! ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱትን÷ ምልክቱንም፡ በግምባራቸው ላይ ያልጻፉትን÷ በእጆቻቸውም ያልተቀበሉትን አየሁ! እኒህ፡ ከክርስቶስ ጋር፡ በዚህ ሺ ዓመት፡ ሕያዋን ኾነውና ነግሠው ይኖራሉ! የቀሩቱ ሙታን ግን፡ ይህ ሺ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ፡ ተነሥተው በሕይወት አይኖሩም፡፡ ይህ፡ በመንፈስ ትንሣኤ የምትገኘው፡ የፊተኛዪቱ ሕይወት ናት! አስቀድማ በምትመጣው፡ በዚች ሕይወት፡ ዕድል ፈንታ ያለው፡ ብፁዕና ቅዱስ ነው! ኹለተኛው ሞት፡ በእኒህ ላይ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ሥልጣን የለውምና! የእግዚአብሔርና የክርስቶስ አገልጋዮች ይኾናሉ እንጂ! ከእርሱም ጋር፡ ይህን ሺ ዓመት ይነግሣሉ!*

*"ሺሁም ዓመት ሲፈጸም፡ ሰይጣን ከእሥራቱ ይፈታል! በአራቱም፡ በምድር ማዕዘናት ያሉትን አሕዛብ÷ ጎግንና ማጎግን እንዲያስታቸው÷ ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል፤ ቁጥራቸውም፡ እንደባሕር አሸዋ የሚያህል ነው፡፡ ወደምድርም ስፋት ወጡ! የቅዱሳን መሰባሰቢያ የኾነችውንም ቅድስት አገር (ኢትዮጵያን) ከበቡ! ከዚህ በኋላ፡ ከሰማይ÷ ከእግዚአብሔር ዘንድ፡ እሳት ወርዳ በላቻቸው! ያሳታቸውም ዲያብሎስ፡ አውሬውና ሓሰተኛው ነቢይ ወደሚገኙበት፡ ወደእሳቱና ወደዲኑ ዐዘቅት ተጣለ! በዚያም፡ ለዘለዓለም እስከዘለዓለም፡ በመዓልትና በሌሊት፡ ሲሠቃዩ ይኖራሉ፡፡"* [፻፬]

## ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
### ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን።
### ስለፊተኛውና ስለኋለኛው ትንሣኤ።

---

ከዚህ በላይ ከሠፈረው የእግዚአብሔር ቃል: አያሌ ቁም ነገሮችን መቅሠም ይቻላል፤ ይኹን እንጂ: ለጥያቄያችሁ ምላሽ ለመስጠት: በተለይ: ትንሣኤ ሙታንን በሚመለከተው ላይ ብቻ እናተኩራለን፤ ይህም: ኹለት ትንሣኤዎች እንዳሉ የሚያመለክተውን ነው። የመጀመሪያው ትንሣኤ: በሕይወተ ሥጋ እያሉ: በቅዱሱ ኪዳን ጸንተው የሚገኙ: የእግዚአብሔር ወገኖች: ለሺ ዓመታት: "ብፁዓን" ተብለውና በፊተኛው የመንፈስ ትንሣኤ ተነሥተው የሚኖሩት ሕይወት ሲኾን፥ ኹለተኛው ትንሣኤ ደግሞ: በመጨረሻ: በክርስቶስ ምጽአት ጊዜ: በመንፈሳዊው የትንሣኤ አካል: ለዘለዓለም የሚነሡት: የኋለኛው ትንሣኤ ነው፤ እኒህ የእግዚአብሔር ወገኖች: በፊተኛው የመንፈስ ትንሣኤ: በሕይወተ ሥጋ እየኖሩ ሣሉ: ምናልባት: የክርስቶስ ምጽአት የኾነ እንደኾነ: በቅጽበት ተለውጠው: ለዘለዓለማዊው የሕይወት ትንሣኤ የሚበቁ መኾናቸውን: መለኮታዊው ቃል ያመለክታል።

በዚሁ መለኮታዊ ቃል መሠረት: በአንድ በኩል: የእግዚአብሔር ወገኖች: ይህን በመሰለ የብቅዓት ሕይወት ላይ ሲገኙ: በሌላ በኩል ደግሞ: የቀሩት የሰው ዘሮች: ቅዱሱን ኪዳን ለመቀበል ፈቃደኞች ባለመኾናቸው፥ የተቀበሉትም: በእርሱ ላይ: ክህደትና ዓመፅ በመፈጸማቸው: በሕይወተ ሥጋ እያሉ: እንደሙታን ይቆጠራሉ፤ ራሳቸውንም: በፈቃዳቸው: ከእግዚአብሔር ሕይወት አግልለው: ለሰይጣን ወገንነት ስላቀረቡ: በክርስቶስ ምጽአት ጊዜ: በሕይወተ ሥጋ የሚገኙት ጭምር: በፃዕር: የመጀመሪያውን የሞት ጽዋቸውን ከተቀበሉ በኋላ: ኹለተኛውንና ነፍሳዊውን ሞት ለሚያስከትልባቸው: ለዘለዓለማዊው የኵነኔ ትንሣኤ ይነሣሉ።

**ጥያቄ:-** *ይህ ነገር: ምሥጢርነቱ: አሁንም: እየረቀቀብን ነውና: እስኪ: ማብራሪያህን አስፋፍተህ ቀጥልልን!*

**መልስ:-** ይህን ምሥጢር በበለጠ ለመረዳት: ዛሬ: በሕይወተ ሥጋ የሚኖር: የአንድ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊን ሕይወት: በማስረጃነት መመልከት ይበቃል። በመንፈስ ቅዱስ: የእግዚአብሔር ልጅ የመኾንን ጸጋ: በምሥጢረ ጥምቀት የተቀበለው: ይኸው ኢትዮጵያዊ: በምሥጢረ ቍርባን ደግሞ: ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር: በሥጋና በደም ስለተዋሐደ: ራሱን: ዘወትር: በንስሓ እያነጻ: ሥጋውን ደሙን እየተቀበለ የሚኖር ከኾነ: በክርስቶስ ትንሣኤ ምክንያት: ዛሬ: በዚህ ዓለም: ከሞት ወደሕይወት ተሸጋግሮ: የመጀመሪያውን የመንፈስ ትንሣኤ ተነሥቷል፤ ኋላም: በመጨረሻው ትንሣኤ: አዲሱን የትንሣኤ አካል ለብሶ ይነሣል።

እንዲህ ከኾነ: ቀደም ብለው የተጠቀሱት: የእግዚአብሔር ቃላት: ለዚህ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ እንደተፈጸሙለት ይረጋገጣል። ይህም: "ኢትዮጵያዊው: ከሥጋና ከነፍስ ሞቶች ነጻ በሚያደርጉት: በኹለቱ ትንሣኤዎች ተነሥቶ: የእግዚአብሔር ልጅና የመንግሥቱ አገልጋይ፥ የዘለዓለም ሕይወትም ወራሽ ለመኾን የሚያበቃውን ጸጋ ተቀዳጅቷል!" ማለት ነው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

*አዎን! የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መቀበል፡ ከእርሱ ጋር፡ በሥጋና በደም ብቻ ሳይኾን፡ በነፍስና በመንፈስም፡ ፍጹም ውሕደትን ማግኘት ስለኾነ፡ ኢትዮጵያዊው፡ ዛሬ፡ በሕይወተ ሥጋ እያለ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ እንደበት፡ "ሙታን" ከተባሉት፡ የማያምኑ ወገኖች መካከል፡ በመንፈስ ተለይቶ ተነሥቷል። ይህ፡ የመጀመሪያው ትንሣኤ ሲኾን፡ በዚህ ትንግርት፡ "እውነት እውነት እላችኋለሁ! ሙታን፡ የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፡ እርሱም፡ አሁን ነው፡ የሚሰሙትም፡ በሕይወት ይኖራሉ።" ያለው፡ መለኮታዊው ቃል፡ ደርሶ የተፈጸመለት መኾኑ ይረጋገጣል።*

*የተፈጸመለት መኾኑ የሚረጋገጠውም፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ፡ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ልጅ የኾነው፡ ይኸው ኢትዮጵያዊ፡ በእርሱ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖና ራሱን፡ በዘወትር ንስሓ በማደስ፡ ሥጋ ወደሙን እየተቀበለ ስለሚኖር፡ ዮሐንስ በራእዩ፡ "በፊተኛው ትንሣኤ፡ ዕድል ያለው፡ ብፁዕና ቅዱስ ነው!" ብሎ ባስተላለፈልን መልእክቱ ስለመሰከረ ነው። ይኸው እውነተኛ ኢትዮጵያዊ፡ ነፍሱ፡ ከመጨረሻው ትንሣኤ በፊት፡ ከሥጋዋ የተለየች ከኾነ፡ እስከዚያን ጊዜ፡ በገነት ተድላ ቆይታ፡ በአዲሱ፡ የክርስቶስ አካል፡ በክብር ይነሣል፡ ይህም፡ "በመቃብር ያሉቱ ኹሉ፡ [የእግዚአብሔርን ልጅ] ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፡ መልካም ያደረጉ፡ ለሕይወት ትንሣኤ፡ ክፉ ያደረጉም፡ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉ!" በሚለው የጌታ ቃል ተረጋግጦለታል። ይኸው ቃል፡ እንደምትመለከቱት፡ በሕይወተ ነፍስ ላሉትና በመጨረሻው ትንሣኤ ለሚነሡት ኹሉ የሚጸና በመኾኑ፡ ነፍስም፡ የማትጠፋ ስለኾነች፡ ክፉዎችም፡ የእምነታቸውን የሥራ ዋጋ መክፈል ስላለባቸው፡ በሲዖል ሥቃይ ቆይተው፡ በውርደት መነሣታቸው አይቀርም።*

ይህን እውነታ፡ በበለጠ ላብራራላችሁ! መነሻው፡ የክርስቶስ ልደት ኾኖ የሚታሰበው፡ ኹለተኛው ሺ ዓመት፡ መቈጠር ሳይጀምር፡ እነሆ፡ አሁን ባለንበት፡ በአንደኛው ሺ ዓመት ውስጥ፡ ኢትዮጵያዊው፡ በክርስቶስ በኵርነት በተጀመረው፡ በፊተኛው ትንሣኤ፡ መንፈሳዊዉን ትንሣኤ ተነሥቶ፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋ እያለ፡ ከክርስቶስ ጋር ነግሦ ይኖራል።

በዚህ፡ በፊተኛው ትንሣኤ፡ በመንፈሳዊ አካሉ ተነሥቶና ከሞት ወደሕይወት ተሻግሮ፡ እንዲህ በሕያውነት የሚኖረው፡ ይህ ኢትዮጵያዊ፡ ዛሬ ገዝፎ የታየበትና ምድራዊ ልብሱ ኾኖ የቈየው ሥጋው፡ ወደመቃብር ቢወርድም እንኳ፡ ኹለተኛው ሞት፡ በእርሱ ላይ ሥልጣን ሳይኖረው፡ በገነት የቆየችው ነፍሱ፡ የዘለዓለምን ሕይወት ትወርስ ዘንድ፡ በመጨረሻው ትንሣኤ፡ እንደክርስቶስ፡ አዲሱን ሰማያዊ አካል ለብሳ ትገለጣለች።

**እስካሁንና ወደፊት፡ ኢትዮጵያዊውን፡ "አንተ"፥ ወይም፡ ኢትዮጵያዊቷን፡ "አንቺ" ስል፡ የማትሞተውን ሕያውት የኾነችውን፡ ሰብአዊት ነፍስ እንጂ፡ በስብሶና ተመልሶ አፈር የሚኾነውን፡ ሥጋዊዉን አካል አለመኾኑን፥ እንዲሁም፡ "ኢትዮጵያዊው" ስል፡ "ኢትዮጵያዊቷ"ንም፡ በአንድነት መኾኑን እንዳስተዋላችሁት አምናለሁ።**

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን።

### የምሥጢረ ትንሣኤ ነገር ሲጠቃለል።

ጥያቄ፦ *እስካኹን የሰማነውን፡ የምሥጢረ ትንሣኤን ነገር፡ እስኪ፡ በአጭር ሓተታ አጠቃልልን!?*

መልስ፦ የምሥጢረ ትንሣኤን ነገር፡ እንዳጠቃልልላችሁ ከጠየቃችሁኝ፡ በተቻለኝ ዓቅም፡ ፈቃዳችሁን ለመፈጸም፡ ከዚህ በሚከተለው ሓተታ ልሞክር! እርሱንም፡ በእየራሳችን ሥነ ፍጥረታዊ አቋም ላይ ተመሥርቶ ያለውንና ገዝፎ የሚታየውን ምስክርነት በሚያመለክተው የመጽሓፍ ቃል እጀምረዋለሁ፤ ይኸውም፡ *"እግዚአብሔር አምላክ፡ ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም፡ የሕይወት እስትንፋስን፡ 'እፍ!' አለበት፤ ሰውም፡ ሕያው ነፍስ ያለው ኾነ!"* ተብሎ የተጻፈው ነው፤ በዚህ ቃል መሠረት፡ ሰው፡ በአካለ ሥጋውና በደመ ነፍሱ፡ የመሬታዊነትና የእንስሳዊነት፡ ማለትም፡ የግዙፍነትና የሟችነት ተፈጥሮ ያለው ሲኾን፤ በአካለ ነፍሱና በመንፈሳዊው የእግዚአብሔር ልጅነቱ ደግሞ፡ የሰማያዊነትና የመልአካዊነት፡ ማለትም፡ የረቂቅነትና የሕያውነት ባሕርይ ያለው መኾኑ ተረጋግጦ ይታወቃል። በዚህ ውይይታችን፡ የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ፡ ይህ ኹሉ፡ ተብራርቶ እንደነበረ፡ ታስታውሳላችሁ።

ይኸው ፍጡር፡ በዚህ ዓለም በሚኖርበት ጊዜ፡ የሰውነቱ ግዙፍ አካል፡ ዘወትር፡ በምግብ ቢጠግብ፥ በመጠጥ ቢረካ፥ በልብስ ቢያጌጥ፥ ጤናማ ቢኾን፥ ተዝናንቶ ቢቀመጥና ፍላጎቱ ኹሉ ተሟልቶለት የተመቸው ቢኾንም እንኳ፡ እግዚአብሔር በቃሉ፡ *"ወደወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ፡ በፊትህ ወዝ፡ እንጀራን ትበላለህ!"* ብሎ፡ ለመጀመሪያው ሰው እንደተናገረው፡ አልፎ አልፎ፡ ያልታሰበ ፈተናና መከራ እየደረሰበት፡ መራቡ፥ መጠማቱ፥ መታረዙ፥ መታመሙ፥ መታሠሩ፥ ወይም መንከራተቱ፡ ማለትም፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ ከእነዚህ ጠንቆች፡ አንዱ፥ ወይም፡ ጥቂቱ፥ ወይም፡ አብዛኛው፥ ወይም፡ ኹሉም ደርሰውበት፡ በችግር መሠቃየቱ አይቀርም። ዕድሜውም ከተገኘ፡ የኋላ ኋላ፡ ማርጀት፥ መድከም፥ በመጨረሻም፡ በሥጋው፡ መሞት፡ መቀበርና በስብሶ፡ ወደአፈርነት መመለስ፡ የማያልፈው፡ ጽዋው ነው። በዚህ ጊዜ፡ *"አፈር ነህና፡ ወደአፈርነትህ ትመለሳለህ!"* የሚለው አምላካዊ ቃል ይፈጸማል።

ይህ ሰው፡ በሥጋ ብቻ የኖረ ከኾነ፡ መቃብሩ፡ ለሥጋው ብቻ ሳይኾን፡ ለነፍሱ ጭምር፡ "ሲዖል" ኾኖ፡ ያች ነፍስ፡ ከሥጋዋ መቃብር ይልቅ፡ እጅግ ጥልቅና ረቂቅ ወደኾነው የጨለማ አዘቅት ወርዳ፡ በዚያ፡ እስከመጨረሻው ትንሣኤ ትቆያለች።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

ይህም ማለት፡ የዚህ ሰው አካለ ነፍስ፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋ ሣለች፡ ምርጫዋ፡ የዚህን የሥጋዊዉንና የደማዊዉን አካሏን ፍላጎት መከተልና ለእርሱ ፈቃድ መገዛት ብቻ ከኾነ፡ ከዚህ መንገዷም፡ ልቦናዋን፡ በእምቢተኛነት አደንድናና በንስሓ "አልመለስም!" ብላ፡ የሞት ጽዋዋን የተቀበለች ከኾነ፡ ዕጣዋና ክፍሏ፡ ኹነኔዋና ፍጻሜዋም፡ እንደፍላጎቷና ምርጫዋ፡ በመጀመሪያ፡ ወደመቃብርና ወደሲዖል፡ በመጨረሻም፡ ለሰይጣንና ለሠራዊቱ ወደተዘጋጀው፡ ወደገሃነመ እሳት መውረድ ይኾናል ማለት ነው።

ነገር ግን፡ የዚህ ሰው አካለ ነፍስ፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋ ሣለች፡ ምርጫዋ፡ ከሥጋዊውና ከደማዊው ፍላጎቷ ይልቅ፡ ያልተዳደፈውንና ጥንተ ባሕርይዋ የኾነውን፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መከተልና መፈጸም፡ በእርሱም ደስ ተሰኝታ መኖር ከኾነ፡ ዕድል ፈንታዋ፡ በመንፈስ፡ የፊተኛው ትንሣኤ ባለቤት ኾና የቆየችበትን፡ የሰላም ሕይወት፡ መጀመሪያ፡ ለአዳምና ሔዋን ተዘጋጅታ በነበረችው "ገነት"፡ ኋላም፡ "መንግሥተ ሰማያት" በምትባለው በእግዚአብሔር መንግሥት፡ በበለጠ ማዕርግና ክብር መቀጠል ይኾናል።

እዚህ ላይ፡ አበክሬ ላሳስባችሁና አጠንክሬ ላስጠነቅቃችሁ የምፈልገው ታላቅ ቁም ነገር፡ እግዚአብሔር፡ ለእያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡሩ ያበረከተው፡ የምሕረት ጸጋውና የሰጠው የፍርድ ውሳኔ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥና ቤዛነት፡ ለአንደኛውና ለመጨረሻው ጊዜ፡ ተቆርጦ የተሰጠ መኾኑን ነው። ይኸውም፡ "መጽደቅ"፡ ወይም፡ "ወደገነትና ወደመንግሥተ ሰማያት መግባት" የሚባለው ሕይወት የሚገኘው፥ ወይም፡ "መኰነን"፡ ወይም፡ "ወደሲዖልና ወደገሃነመ እሳት መውረድ" የሚባለው ሞት የሚደርሰው፡ እያንዳንዱ ሰው፡ ገና፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋው እያለ፡ ወድዶ፥ ፈልጎና መርጦ በሚከተለው እምነቱና በሚፈጽመው ምግባሩ ምክንያት መኾኑን የሚያረጋግጠው መለኮታዊ ሥርዓት ነው።

ይህ ኹኔታ፡ ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ የነበረ መኾኑ፡ በአዳምና ሔዋን፡ የሕይወትና የሞት ታሪክ ተረጋግጧል። እነርሱ፡ በእግዚአብሔር ቃል፡ የተሰጣቸውን ሥርዓት፡ አክብረው የጠበቁት እንደኾነ፡ ለዘለዓለም፡ ሕያው ኾነው እንደሚኖሩ፥ ያልጠበቁት እንደኾነ ግን፡ ሞትን እንደሚያስከትልባቸው፡ ከራሱ፡ ከፈጣሪያቸው አስቀድሞ በተነገራቸው ማስጠንቀቂያ ተረድተውት ነበረ፤ ያን፡ መልካም የኾነውን ሥርዓት የተላለፉትም፡ የሚደርስባቸውን ውድቀት እያወቁ፡ በራሳቸው ፍላጎትና ባደረጉት ምርጫ መኾኑ ታይቷል።

እውነተኛው ኢትዮጵያዊ ግን፡ ኃጢአቱ የተሠረየባትንና ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ የተወለደባትን የክርስትና ጥምቀቱን፡ በእምነት አጽንቶ፥ የዘወትር ኃጢአቱንም፡ በንስሓ እያጠራና የክርስቶስን ሥጋና ደም እየተቀበለ ከኖረ፡ ከፈጣሪው ጋር ያለውን ቃል ኪዳን፡ በበኩሉ፡ በትክክል መፈጸሙ ነውና፡ በቃል ኪዳኑ የታመነው አምላክ ደግሞ፡ ለዚህ ኢትዮጵያዊ፡ የበኩሉን፡ የቸርነቱን ሥራ ያደርግለታል።

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን።

### የምሥጢረ ትንሣኤ ነገር ሲጠቃለል።

ይኸውም፡ በቃል ኪዳኑ የታመነው አምላክ፡ ለዚሁ ኢትዮጵያዊ፡ ዛሬ፡ የመንፈስ ትንሣኤን ተቀዳጅቶ፡ በዚያ ሕይወት የመኖርን መብትና ሥልጣን እንዳጐናጸፈው ኹሉ፡ ኋላም፡ አዲሱን የክርስቶስን የትንሣኤ አካል ለብሶ፡ ለዘለዓለም ሕይወት እንዲነሣ ያደርገዋል። ለዚያ ጸጋ የበቃ ኾኖ፡ በክርስቶስ የዳግም ምጽአት ጊዜ፡ በሕይወተ ሥጋ ከተገኘም፡ በቅጽበታዊ መለወጥ፡ ታድሶ፡ የመጨረሻው ትንሣኤ ባለዕድል ይኾናል።

ለዚህ የትንሣኤ ጸጋ ስለሚያበቃው መለኮታዊ ምሥጢር ለማወቅና ለማስረዳት፡ በተለይ፡ ለዘመናዊው ሰው፡ ብዙም አዳጋች አይኾንም፡ ምክንያቱም፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ሰብአዊው የሥነ እውቀት ጥበብ፡ እጅግ ከመራቀቁ የተነሣ፡ ያስገኘውን ትንግርታዊ የሥልጣኔ ውጤት፡ በቀላሉ፡ በምሳሌነት ለማቅረብ ስለሚቻል ነው፡ ይኸውም፡ ፍጥረታዊው ሰው፡ በመንኰራኵር፡ ወደኅዋ መጥቆ ለመኼድ፡ በቅድሚያ፡ ጠፈረተኞች፡ ሊያውቁት በሚያስፈልጋቸው የሙያ ሥልጠና ሊደረጅ፡ ሊለብሱት በሚገባቸውም ልዩ ትጥቅ ተከናውኖ ሊገኝ እንዳለበት፡ አለዚያ፡ ከመሬትም እንኳ ሊነሣ እንደማይቻለው ይታወቃል፡ እንደዚሁ ኹሉ፡ ሃይማኖታዊው ሰው፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋ እያለ፡ ለመጀመሪያው የመንፈስ ትንሣኤ፡ ከዕረፍተ ሥጋውም በኋላ፡ ለነፍስ የሣልስት ትንሣኤና የአርባ ቀን ዕርገት ዕድል ለመብቃት፡ በምሥጢረ ጥምቀት ጊዜ፡ ከእግዚአብሔር፡ የተወለደበትንና በኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘውን፡ በንስሓና በቅዱስ ቍርባን ተጠብቆ የኖረውንም፡ ያን፡ መንፈሳዊ አካል፡ ሊለብስ የሚገባው ለመኾኑ፡ አያጠያይቅም። ረቂቁን የትንሣኤን ምሥጢር፡ እንዲህ አድርጎ አግዝፎ፡ በቀላሉ ለማስረዳትና ለመረዳት፡ "አስቸጋሪ አይኾንም!" የሚያሰኘው፡ ይህ የዘመኑ ሥጋዊ ጥበብ ያስገኘው ክሥተት ነው።

እንግዲህ፡ እውነተኛው ኢትዮጵያዊ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የተቀዳጀው፡ የመጨረሻው የጸጋ ዘውድ፡ ለዘለዓለም፡ በሕይወት ይኖር ዘንድ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ የመኾንን ክብር፡ ማግኘቱ ሲኾን፡ በሕይወተ ሥጋ ሣለም፡ ረቂቃን የኾኑትን ጠላቶቹን ጭምር አሸንፎ፡ እንዲደርስበት የተሰጠው፡ የመጨረሻው የድል ምዕራፍ ደግሞ፡ ትንሣኤ ነው። ስለዚህ፡ የዚህ ኢትዮጵያዊ፡ የመኖር ፍጻሜው ወይም ግቡ፡ መሞት ሳይኾን፡ መነሣት ስለኾነ፡ ከእርሷ እንዳይደርስ የሚቃወመውን፡ የዲያብሎስን የክፋትና የኃጢአት ኃይላትን እየተቋቋመ፡ በዓይነ ሕሊናው የሚያየው፤ በእዝነ ልቡናው የሚሰማውና በግእዘ አእምሮው የሚያስበው፡ የትንሣኤን እንጂ፡ የሞትን ነገር አይደለም፤ ማለትም፡ አተኩሮ የሚመለከተው፡ መድረሻውን፡ ትንሣኤን እንጂ፡ መሸጋገሪያውን ሞትን አይደለም። ይህም፡ ከዓቢይ ጾም ጀምሮ፡ በሕማማት ሱባዔ ሰሞን፡ ይደርስባት ዘንድ፡ አርቆ የሚያያትና በናፍቆት የሚጠባበቃት፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ የስቅለት ሞቱ የተፈጸመባትን፡ ዕለተ ዓርብን ሳይኾን፡ የትንሣኤው ብርሃን ያንፀባረቀባትን፡ የዕለተ እሑድን መንፈቀ ሌሊት በመኾኑ ይታወቃል።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

በእውነተኞች ኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ሞት፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ፡ የሚፈራ መኾኑ ቀርቶ፡ የሚናፈቅ የኾነው ፡ ደግሞም፡ በሥጋ ሞት የሚለዩዋቸውን ወገኖቻቸውን፡ "እንቀላፉ! ዐረፉ!" ብለው፡ በሰላም የሚሸኟቸው ፡ የዚህኑም የዕረፍታቸውን ሣስተኛ ቀን፡ "ሣልስት" ብለው፡ እንደክርስቶስ ትንሣኤ ፡ አርባኛውንም ቀን፡ እንደክርስቶስ ዕርገት አድርገው፡ በመንፈሳዊ ይባቤና በማኅሌት እንዲኾን፡ ሥርዓት የሠሩት፡ በዚህ ምክንያት መኾኑን፡ እናንተም ተገንዝባችሁት፡ ይህን ሥርዓት፡ አክብራችሁ፡ ልትፈጽሙት ይገባችኋል። እስዚያ፡ እግዚአብሔር፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ኾኖ፡ በቤዛነት የሠዋው፡ ያ ኹሉ ድካሙ፡ ለከንቱነት እንደተጻረገ፡ ሃይማኖታችሁና እርሷን በሚመለከት፡ እስካሁን ያገኛችሁት ትምህርትም፡ በየራሳችሁ ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ በማያምኑ ወገኖች ዘንድ ጭምር፡ ለከንቱ ውዳሴ እንደምትጠቀሙበት ተደርጎ እንደሚገመት ማወቅ አለባችሁ።

### በትንሣኤ ብርሃን ያሸበረቀውን
### የቀብር ሥርዓታችንን እናጨልመው!

ጥያቄ፦ ሊኾን የሚገባው እንዲህ ከኾነ፡ ማለትም፡ "የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን፡ በሥጋ ሞት የሚለዩዋቸውን ወገኖቻቸውን፡ 'እንቀላፉ! ዐረፉ!' ብለው፡ እንዲህ፡ በሰላም የሚሸኟቸው ከኾነ፡ የዚህኑም የዕረፍታቸውን ሣስተኛ ቀን፡ 'ሣልስት' ብለው፡ እንደክርስቶስ ትንሣኤ ፡ አርባኛውንም ቀን፡ "ሕርባ" ብለው፡ እንደክርስቶስ ዕርገት፡ በመንፈሳዊ ይባቤና በማኅሌት እንዲኾን፡ ሥርዓት ከሠሩ"፡ ታዲያ፡ ለምንድር ነው፡ ይህ ሥርዓት፡ በዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ ዘንድ ሲፈጸም የማይታየው? በተግባር ላይ ውሎ፡ እያየን ያደግነውና ዛሬም ለፍኖ የምናየው፡ የዚህን ሥርዓት ተቃራኒ ገጽታውን ነው፤ ማለትም፡ በመሪር ኀዘንና ተስፋ በመቍረጥ ማልቀስን፡ ጥቍር ልብስ መልበስንና የመሳሰለውን የቍጭትና የብስጭት፡ ራስንም የመጕዳት ድርጊት መፈጸምን፡ ከዚያም አልፎ፡ በእግዚአብሔር ላይ እሮሮ ማሰማትን ነው።

በዚህም ድርጊታችን፡ በአዋጅ የታዘዝን ይመስል፡ በሕይወተ ሥጋ ቆሞና ኵልኵሎ፡ ተራውን ለሚጠብቀው፡ ለማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር፡ በኢትዮጵያዊነታችን፡ የምናስተላልፈው መልእክት፡ ሞት፡ በሰው ላይ ያለው፡ የገዢነት ኃይልና ሥልጣን የቀጠለ ስለኾነ፡ አስፈሪነቱን፥ አሠቃቂነቱንና ጨካኝነቱን እንጂ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የተገኘውን፡ የዘለዓለም ሕይወትንና የድል አድራጊነትን ብርሃናዊ ደስታን አይደለም። እንዲህ ያለው ሥርዓት እያለን፡ እንዴት፡ ይህን የመሰለው አስከፊ ልማድ ጸንቶ ሊቀጥል እንደቻለ፡ እጅግ ያሳዝናል፥ ያስገርማልም።

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::
## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን::
### በትንሣኤ ብርሃን ያሸበረቀውን የቀብር ሥርዓታችንን፡ ለናጨልመው!

---

*ስለዚሁ ጠንቀኛ ልማድና ስለመፍትሔውም፡ በማብራራት፡ መልካም የኾነውን፡ የህልውናችንን መሠረታዊ አቋም፡ እንዲህ፡ የሚያናጋውን፡ መንፈሳችንንም የሚያናውጠውን፡ የየሕሊናችንን ጸጥታ የሚያውከውንና በጎውን ሥርዓታችንን የሚያተረግምሰውን፡ የየልባችንን ጭንቀት፡ ጨርሰን እናስወግደው ዘንድ፡ እስኪ፡ አባክህ፡ የተላመድነውን፡ የምሥራች መልእክትህን አስሰማን!?*

መልስ:- ከእግዚአብሔር ፍርሃት ይልቅ፡ የሰው ይሉኝታ አይሎብን፡ ከፈጣሪያችን የሕይወት ቃል ይልቅ፡ የዲያብሎስ የሞት ትእዛዝ በልጦብን፡ የተወገደውንና የሌለውን ይህን፡ የኀዘንና የለቅሶ ችግር የፈጠርነውኮ እኛው፡ እየራሳችን ነን:: እንደቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችንማ፡ "እምነንብሃል!" ያልነውን አምላካችንን፡ በእውነት የመፍራቱና የማክበሩ፡ የመታዘዙም ሃይማኖታዊው ፍላጎት፥ ምግባራዊውም ልማድ ኖሮንማ ቢኾን፡ ይህን የመሰለው ኹኔታ አይታይብንም፥ ድርጊቱም አይፈጸምም ነበር፡ ነገር ግን፡ የእግዚአብሔሩ ፍቅርና የሃይማኖቱ ቅንዓት፡ በትውልዱ ዘንድ ስለሌለ፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ፡ ሴትም ኾነች ወንድ፡ ራሱ ፈጣሪ፡ መሥዋዕት ኾኖ ካቃለለት፡ ከዚህ ረቂቅ ሸክም፡ እየራሱን ነጻ ለማውጣት እንኳ ፈርቶ፡ ይኸው ክፉው ልማድ፡ ስር ሰድዶና በጽናቱ ቀጥሎ፡ በተንበርካች፡ እያሠቃየው ሲኼድ ይታያል፡ ከዚህ የተነሣም፡ እነሆ፡ ፈጣሪያችንን፡ ከነእናቱ ስናሳዝን እንኖራለን::

ራሱ አሳዛኝ የኾነው፡ የዛሬው ኢትዮጵያዊ የኀዘን ወግ፡ ምን ዓይነት እንደኾነ፡ በአለባበሳችን ሳይቀር፡ ጎልቶ ይታያል፡ ይኸውም፡ "ኀዘን" የሚባለው፡ የማይቀረው ጽዋ፡ በየዕድሜአችን መካከል በሚደርስብን ጊዜ ኹሉ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ልንለብሰውና ልንጎናጸፈው የሚገባን የልብስና የሸማ ዓይነት፡ ቀለሙ፡ "ጸንዳ" (ነጭ) መኾን ሲገባው፡ ያ ቀርቶ፡ ወደጥቁርነት እንዲለወጥ በመደረጉ ነው:: እርግጥ! ኢትዮጵያዊው የአለባበስ ሥርዓት፡ እንደማናቸውም ሌላው ኢትዮጵያዊ ሥርዓት፡ የተመሠረተው፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ላይ ስለኾነ፡ ለደስታም ኾነ ለኀዘን፡ ምንጊዜም፡ ነጭ የኾነበት ምክንያት፡ በቂ የኾነ የራሱ መነሻ አለው፡ ይህም፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በተገኘው ጸጋ፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ፡ ከሓሰት ጨለማ፡ ወደእውነት ብርሃን፥ ከኃጢአት ባርነት፡ ወደጽድቅ ነጻነት፡ ከዲያብሎስ ገዥነት፡ ወደእግዚአብሔር ልጅነት፥ በመጨረሻም፡ ከዘለዓለም ሞት፡ ወደትንሣኤ ሕይወት የመሸጋገሩ ምሥጢር እውን የኾነበት፡ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱ ነው::

አዎን! እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ሰው ኾኖ፡ ፍጥረቱን ኹሉ ባዳነው፡ በእግዚአብሔር ልጅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ድል አድራጊነት የተገኘውን፡ የዘለዓለምን ሕይወት ብርሃናዊ ጸጋ የተላበስን መኾናችንን ለማረጋገጥ፡ በኀዘናችን ጊዜ ሳይቀር፡ ነጭ ልብስ እንለብሳለን፤ የሚች ቤተሰብም፡ በያንገታቸው፡ ነጭ ክር ያሥራሉ::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

በኃዘን ወቅት፡ ለምልክት እንዲኾን፡ ሴቶቹ፡ ኩታቸውን አጥፈው፡ በጥለቱ በኩል በመከናነብ ይለብሱታል፤ ወይም፡ የኩታቸውን ጥለት፡ አንዱን ወገን፡ በወገባቸው ላይ ታጥቀው፡ ሌላውን ወገን ደግሞ ይከናነቡታል፤ ዋናዎቹ ኀዘንተኞች ግን፡ ወደአንገታቸው አጣፍተው፡ ከደረታቸው ላይ ይቋጥሩታል፡ ይህ፡ የተለያየው አለባበስ፡ "ማሸረጥ" ይባላል።

ይኹን እንጂ፡ የዛሬው ትውልድ፡ በብሩህነት ያሸበረቀውን፡ ይህን የመሰለውን፡ ፍጹም የሠመረ ኢትዮጵያዊ የአለባበስ ሥርዓት ትቶ፡ ግብፃውያንና አውሮጳውያን፡ ለክብርና ለበዓል፡ ለደስታና ለኀዘን ጊዜያቸው በሚገለገሉበት፡ በጽልመታዊው የአለባበስ ባህል በመተካቱ፡ ምን ዓይነት ውርደትና ውድቀት የደረሰበት ይመስላችኋል? የራሱ የኾነውን፡ መልካሙን ቅርስ፡ ከቤተ ክህነቱና ከቤተ ምልክናው ጀምሮ፡ በቤተ ሕዝቡም ዘንድ ጭምር እንዲናቅና እንዲዋረድ፥ እንዲጠላም ማድረጉ ብቻ ሳይኾን፡ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን፡ እውነተኛ ማንነትና ምንነት መቀየሩን፡ በአዋጅ አረጋግጦ ማሳወቁ አይደለምን? ይህን እውነታ፡ ሌላው እንኳ ባይኾንለት፡ እናንተ፡ በማስተዋል ልትመለከቱትና ተገቢውን ልታደርጉ ይገባችኋል።

በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱና ሥርዓቱ ጸንቶ የሚገኘው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፡ ከከተሜው ይልቅ የገጠሩ፡ እስከዛሬና ዛሬም ቢኾን፡ እያደረገ እንደሚታየው፡ ነጭ ልብሱን ተጐናጽፎ የሚወጣው፡ በክብር፡ በበዓልና በደስታው ቀን ብቻ ሳይኾን፡ በኃዘኑም ጊዜ መኾኑ፡ በቀ የኾነ፡ ሃይማኖታዊ ምክንያት እንዳለው፡ ቀደም ብዬ ገልጬላችኋለሁ፤ ይህም ምክንያት፡ በዲያብሎስ መሣሪያነት የገባው ሞት፡ ከመቃብርና ከሙስናው ጋር፡ "እነሆ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ተወገደ!" በማለት፡ ብርሃን ተጐናጽፈውና ነጭ ልብስ ለብሰው፡ ትንሣኤውን፡ ለእነማርያም መግደላዊት ባበሠሩት የመላእክቱ ምሥራች መልክ፡ ዛሬም፡ በእውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን ዘንድ እየተፈጸመ በሚገኘው፡ ፀዓዳ በኾነው የአለባበስ ሥርዓት ተረጋግጦ ይታያል።

አዎን! እያንዳንዱ፡ በሕይወተ ሥጋ ቋሚ የኾነው ምእመን፡ ያ፡ ከሥጋ ቁራኝነት ተላቅቆ ያረፈው ምእመን፡ "ሞት፥ መቃብርና ሙስና ሳያገኘው፡ በክርስቶስ፡ የትንሣኤ ልጅ ኾኖ፡ ህልውናውን፡ በዘለዓለም ሕይወት በመቀጠል ይኖራል!" የሚል መልእክት ያለውን፡ የምሥራች ድምፅን ለመስማትና ለማሰማት፡ በፍትሓተ ጸሎቱ ሥርዓትና በቀብሩ በዓል ላይ፡ ነጭ ልብሱን ለብሶ ይገኛል፤ የሣልስቱና የአርባው ቀኖች ሥርዓትም፡ በዚሁ፡ በክርስቶስ ትንሣኤና ዕርገት ምሥጢራት ላይ ተመሥርቶ ይፈጸማል።

የዛሬው ትውልድ ግን፡ በሌሎቹ ድርጊቶቹ ኹሉ እንደሚታየው፡ የሚያዳምጠውና የሚከተለው፥ የሚያደርገውም፡ አምላኩና መሪው ኢየሱስ ክርስቶስ ያለውንና ያደረገለትን ሳይኾን፡ የዚያን ተቃራኒ፡ ማለትም፡ ባዕድ የኾነውን፡ የዲያብሎስን ቃልና ተግባር መኾኑን፡ ይኸው፡ በየጊዜያቱና በየምክንያቱ፥ በየቦታውም፡ በገሃድ እየቀጠለ ያለውን ውሎ እንመለከተዋለን።

# ምዕራፍ ፫፡ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::

## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን::

### በትንሣኤ ብርሃን ያሸበረቀውን የቀብር ሥርዓታችንን እናጨልመው!

---

ይህ እውነታ፡ ከሌላው ኹሉ ኹኔታ ይልቅ፡ በይበልጥ፡ ተረጋግጦና ገዝፎ የሚታየው፡ ያው፡ በታወቀው፡ በለቅሶአችንና በኀዘናችን ጊዜ በሚለበሰው ጥቁር ልብስና በሚፈጸመው የዋይታ ድርጊት ነው:: ይኸውም፡ "ሕያዋን ነን" የሚሉት፡ ቋሚ ወገኖቹ፡ በዚያ፡ በጥቁር ልብሳቸው ተሸፋፍነው፡ ያን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፡ የብርሃን ልብስ ተጎናጽፎና በብርሃናውያን መላእክት ታጅቦ፡ ወደዘለዓለም ሕይወት እየገባ ያለውን፡ ምእመን ወገናቸውን፡ ልክ፡ እጅና እግሩን ታሥሮ፡ በጨለማም ዐጽፍ ተጠቅልሎ፡ ለዲያብሎስና ለሠራዊቱ ወደተዘጋጀው፡ ሲያልና ገሃነም ሊገባ ሲኼድ፡ ተሰብስበው እየሸኙት መስለው መታየታቸው ነው::

በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ በኀዘን ጊዜ ሳይቀር፡ ነጭ ልብስ ተለብሶ፡ የሚካኼደው የአለባበስ ባህል፡ ምክንያቱ፡ ይህ መኾኑ እየታወቀ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በቤዛነቱ መሥርቶ ያጸናውና የቀደሰው፡ ይኸው ኢትዮጵያዊ መልካም ሥርዓት፡ እንዲህ፡ ከኢትዮጵያ እየተወገደና በባዕዳን ጥቁር ልብስ እየተተካ፡ የዲያብሎስ የኾነውም፡ ባዕዱ ልማድ እየሰፈነ እንዲኼድ መደረጉን፡ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስና እናቱ ድንግል ማርያም ሲመለከቱ፡ መልእክታቸው ተቀባይ በማጣቱ፡ የቱን ያህል እንደሚያሳዝናቸው፡ በማናቸውም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ዘንድ ይታመንበታል::

### የእግዚአብሔር ሕያው ታሪኩ መገለጫ::

የኀዘንና የለቅሶ፡ የሞትና የትንሣኤ ነገር፡ እዚህ ላይ ከተነሣ ዘንድ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን፡ በዚህ ረገድ ስላለው፡ ስለማንነታችንና ስለሰውነታችን፡ ያስገኘልንን እውነታ፡ እስኪ፡ ጠለቅ ብለን እንመርምረው! እንደምታውቁት፡ "ታሪክ"፡ ሰዎች፡ ራሳቸው የሠሩትን፡ ያለፈ፡ ያረጀና የሞተ ድርጊታቸውን፡ ራሳቸው መዝግበው የሚነግሩበት ሰብአዊ ዘዴ በመኾኑ፡ እነርሱው፡ ይህንኑ ዘዴ፡ ሥጋዊና ምድራዊ፡ ምውትም ለሆነ የኑሮ ሥርዓታቸው፡ መገልገያ መሣሪያ አድርገው ይጠቀሙበታል:: ስለዚህ፡ ሰዎች፡ እውነተኛነቱ በትክክል ያልተረጋገጠ፡ ይህንኑ ታሪካቸውን፡ ግዑዝ በኾኑ ነገሮች፡ ማለት፡ በብራና፡ በወረቀት፡ በድንጋይ ወይም በብረታብረትና በመሳሰሉ ሰሌዳዎች ላይ እየጻፉ ወይም እየቀረጹ፡ "ታሪክ" ወይም "የታሪክ ቅርስ" በሚል ስያሜ፡ ለትውልድ ያስተላልፉታል::

የእግዚአብሔር ሥራ ግን፡ ዘወትር ሕያው ስለኾነ፡ "ታሪክ" ሊኾን አይችልም፡ አይደለምና ነው:: ስለዚህ፡ መለኮታዊው ሥራ፡ እኒህን ሁሉ አይሻም፡ ባሕርዩ፡ ሕያው ስለኾነ፡ የምውትነት ተፈጥሮ ያላቸው፡ እኒህ ነገሮችና ጥበቦች አይስማሙትም:: የእርሱ መገለጫው ወይም መጻፊያ ሰሌዳው፡ በሕይወት የሚንቀሳቀሰው፡ ራሱ በመልኩ የፈጠረው ሕያው ሰውነት ነው:: እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ሕያው ሰውነታችን፡ እንዲህ የእግዚአብሔር ሥራ መገለጫው ነው ብለን የምናምን በመኾናችን፡ በምግባር የምንገልጸው ይኸው ሃይማኖታችን፡ እነሆ በዚህ አቋሙ ጸንቶ እስካኹን ኖርዋል፤ ዛሬም አለ፤ ወደፊትም ይኖራል::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

የእግዚአብሔር ሥራ፡ እንደሰዎች ታሪክ፡ ትናንት ሳይኖርበት፡ በዛሬነት ብቻ፡ በእያንዳንዳችን የግል ሕይወት ኾነ በብሔራዊ ህልውናችን፡ ዘወትር እየተነበበ፡ ኀልፈት ውላጤ ሳይኖርበት፡ በሕያውነት የሚቀጥል እንጂ፡ "ታሪክ" ተብሎ በቅርስነት፡ ወደቤተ መዛግብት ተወስዶ አይቀመጥም:: በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸውና ምግባራቸው ጸንተው፡ በዕረፍተ ሥጋ የተለዩን፡ የወገኖቻችንም ሕይወት፡ ዛሬ በሕያውነት እየተንቀሳቀሰን፡ ለእግዚአብሔር ሕያው ሥራ፡ መገለጫዎች እንደኾንነው፡ እንደማንኛችንም እውነተኞች ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ሁሉ፡ ሕያው የኾነው የእግዚአብሔር ሥራ፡ በሕያውነት እየተነበበበት፡ በሕያውነት ይኖራል እንጂ፡ ታሪክ ሆኖ ወደመዘክርነት አይተላለፍም::

ለቸሩ እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰውና! እኛም እየራሳችን፡ ቀደም ብለው፡ በዕረፍተ ሥጋ እንደተለዩን ወገኖቻችን እስክንኾን ድረስ፡ ከእያንዳንዳቸው የዕረፍታቸው ዕለት አንሥተን፡ በየሟልስታቸውና በየአርባቸው፥ ከዚያም በኋላ ባሉት ቀኖች፡ እኛ፡ በዓፀደ ሥጋ፥ እነርሱ፡ በዓፀደ ነፍስ በምንገኝበት አኗኗራችን፡ ኹላችንም ሕያዋን ኾነንና ተጽናንተን፡ ዛሬ፡ በመንፈስ፥ በመጨረሻው የሕይወት ዘመን ደግሞ፡ በአዲሱ የትንሣኤ አካል፡ "በደስታና በሰላም፡ አብረን እንኖራለን!" ብለን፡ በእውነተኛው ኢትዮጵያዊነታችን አምነን፡ እነሆ፡ እስካኹን፡ ምድራዊ ህልውናችንን፡ ያለልቅሶና ያለኀዘን፡ ለመቀጠል ችለናል::

በምድራዊው ህልውናችን፡ እንዲህ፡ ለመቀጠል የቻልነው፡ *"እነሆ፡ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው፡ ከእነርሱም ጋር ያድራል፡ እነርሱም ሕዝቡ ይኾናሉ:: እግዚአብሔርም፡ እርሱ ራሱ፡ ከእነርሱ ጋር ኾኖ፡ አምላካቸው ይኾናል:: እንባዎችንም ኹሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፤ ሞትም፡ ከእንግዲህ ወዲህ አይኾንም፡ ኀዘንም ቢኾን፡ ወይም፡ ጩኸት፥ ወይም፡ ሥቃይ፡ ከእንግዴህ ወዲህ አይኾንም::"* የሚለውን እውነተኛውን የሃይማኖታችንን የምሥራች ቃል፡ በእውነተኛ ምግባር፡ እውን ስላደረግነው መኾኑን፡ ከልባችሁ ልትገነዘቡት ይገባል::[፻፮]

እንግዴህ፡ ይህን የመሰለው ጽዋ፡ እስካኹን ያልደረሰበት ሰብአዊ ፍጡር የለምና፥ ወደፊትም በማንኛውም ሰው ላይ፥ በእናንተ፡ በእያንዳንዳችሁ ጭምር መድረሱ አይቀርምና፡ በዚያን ጊዜ፡ እያንዳንዳችሁ፡ ፈተናውን ተቋቁማችሁ፡ በጽናትና በአሸናፊነት ለማለፍ ትችሉ ዘንድ፡ ሃይማኖታችሁን፡ በምግባር ፈጽማችሁ በመገኘት፡ እየራሳችሁን፡ ለሰው ሳይኾን፡ ለእግዚአብሔር እውነት የተዘጋጀና የበቃ እንድታደርጉ፡ አደራ እላችኋለሁ::

# ምዕራፍ ፫፣ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት፡፡
## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን፡፡

### ትክክለኛው የኢትዮጵያውያን የሣልስትና የአርባ ቀን ሥርዓት፡፡

*ጥያቄ፡- ከቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን ውጭ፡ በአረታዊው ልማድ ብቻ እየቀጠለ የኼደውን፡ የሣልስትና የአርባ ኀዘንንና ልቅሶን ነገር በሚመለከት ላቀረብነው ጥያቄ፡ የምትሰጠንን መልስ እንጠብቃለንና፡ ይህንኑ ቍምነገር፡ ከዚህ ጋር አያይዘህ ሳታብራራልን እንዳታልፈው፡ እናስታውስህ ዘንድ ፍቀድልን!*

መልስ፡- እኔም አልዘነጋሁትም፡ አያይዤ ላመጣላችሁ ነው፡ በማስታወሳችሁ ግን፡ የፍላጎታችሁን እውነተኛነትና የንቃታችሁን መጠን እያደነቅሁ፡ በዚህ ኹኔታችሁ፡ እንደገና ላሞግሳችሁ እሻለሁ፡፡

ወደጥያቄያችሁ ርእስ ልመለስና፡ በእኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ዘንድ ያለው፡ እውነተኛውና ትክክለኛው የሣልስትና የአርባ ቀን ሥርዓት፡ የሃይማኖታችንን የምሥራች ዜና ተከትሎ ይፈጸማል፡፡ ይኸውም፡ ከመካከላችን፡ ቀደም ብሎ፡ በዕረፍተ ሥጋ የተለየው ወገናችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤና ዕርገት ልጅ በመኾኑ፡ ነፍሱ፡ በመቃብር ሳትቀር፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፡ ሕያው ሆና የተነሣች፡ በአርባኛውም ቀን፡ እንደፈጣሪዋና ጌታዋ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወደማደሪያዋ ወደገነት፡ ያረገች መኾኗን አምነን፡ ሥጋው፡ ወደመቃብር በወረደበት ሦስተኛ ቀን፡ ሣልስቱን፡ በአርባኛውም ቀን፡ አርባውን፡ በቤተ መቅደሳችን ተሰባስበን፡ ለእግዚአብሔር፡ ምስጋናችንን፡ በመንፈሳዊ ደስታ የምናቀርብበት ሥርዓት ነው፡፡ የዚህ ሥርዓት መሠረቱ፡-

፩ኛ፡ እነማርያም መግደላዊት፡ "በመቃብር ይኖራል!" ብለው ያመኑትን፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋ፡ እንደአረቱ ልማድ፡ ሽቱ ሊቀቡ፤ በሦስተኛው ቀን፡ በእሑድ ማለዳ፣ ወደመቃብሩ መጥተው ሳለ፡ እርሱ ጌታችን፡ ከሙታን ተለይቶ የመነሣቱን ምሥራች፡ ከመላእክት እንደሰሙና እርሱን ራሱን አይተው፡ ትንሣኤውን እንዳረጋገጡ ኹሉ፥

፪ኛም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሦስተኛው ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ፡ ለሐዋርያት፡ አርባ ቀን እየታያቸውና እስከሞት ካደረሰው የመስቀል መከራው፡ ሕያው ኾኖ የመነሣቱን እውነታ፡ በብዙ ማስረጃ እያረጋገጠላቸው፥ ስለእግዚአብሔርም መንግሥት እየነገራቸው፡ አብሩዋቸው ቆይቶ፡ በአርባኛው ቀን፡ እነርሱ እያዩት፡ ወደሰማይ ከፍ ከፍ ማለቱን፥ ደመናም፡ ከዓይናቸው ሠውራ መቀበሏን እንዳረጋገጡ ኹሉ፥

፫ኛ፡ በዚያን፡ በሦስተኛው ቀን ትንሣኤውና በአርባኛው ቀን ዕርገቱ ጊዜም፡ እነማርያም መግደላዊትና ሐዋርያት፡ ፍጹሙንና ዘለዓለማዊውን ደስታ ማግኘታቸውን፡ በእውን እንዳረጋገጡ ኹሉ፡ እኛም፡ ከዚያ፡ በሥጋ ዕረፍት ከተለየን አማኝ ወገናችን ጋር፡ በእየራሳችን፡ ለዚያ ፍሥሓ ተካፋዮች ላደረገን መለኮታዊ ጸጋ መብቃታችንን ማረጋገጣችን መኾኑን፡ እናንተ፡ ራሳችሁ ልትገነዘቡት፥ ለሌላውም፡ ልታስገነዝቡት ይገባል፡፡

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

በሣልስትና በአርባ ዕለታት የሚፈጸሙት፡ እነዚህ ሥርዓታት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤና ዕርገት፥ በሌሎቹም መለኮታውያን ትንግርቶቹ ላገኘናቸው ጸጋዎቻችን ኹሉ፡ በኲር የኾነው፡ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የከፈተልንን ሰማያዊ ጥርጊያ ተከትለን፡ የምናልፍባቸው ጐዳናዎች ናቸው:: ከእነዚህ ጐዳናዎች መካከል፡

የመጀመሪያው:- ለሣልስቱ፡ በዘመነ ትንሣኤ የሚጠቀሰው፡ *"አንሰ ሰከብኩ ወኖምኩ፤ ወተንሣእኩ እስመ እግዚአብሔር አንሥአኒ፤ ኢይፈርህ እምአእላፈ አሕዛብ::"* ትርጉሙ፡ *"እኔ ተኛሁ አንቀላፋሁም፤ እግዚአብሔር አስነሥቶኛልና ተነሣሁ፡ የከበቡኝን አእላፍ አሕዛብ አልፈራቸውም::"* የሚለው ምስባክ ከተዘመረ በኋላ፡ *"ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ:: የሚያምንብኝ፡ ቢሞት እንኳ፡ ሕያው ይኾናል፤ ሕያው የኾነ፥ የሚያምንብኝም ኹሉ፡ ለዘላለም አይሞትም"* ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመቃብር የነበረውን አልዓዛርን፡ ከሞት ባስነሣበት ጊዜ በተናገረው የምሥራች ቃል የተከፈተው ነው::

ኹለተኛውም:- ለአርባው፡ በዘመነ ዕርገት የሚጠቀሰው፡ *"ዐረገ ውስተ አርያም፡ ጼዊወከ ጼዋ፤ ወወሀብከ ጸጋከ ለእጓለመሕያው፤ እስመ ይከህዱ፡ ከመ ይኅድሩ::"* ማለትም፡ *"የካዱት፡ በእርሱ ተመልሰው፡ በዚያ ይድኑ ዘንድ፡ ምርኮን ማርከህ፡ ወደሰማይ ዐረግህ፤ ጸጋህንም ለሰው ልጆች ሰጠህ::"* የሚለው መዝሙር ከተዘመረ በኋላ፡ *"እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያርግ፡ ወደሰማይ ትኲር ብለው ሲመለከቱ ሣሉ፡ እነሆ፡ ነጫጭ ልብስ የለበሱ፡ ኹለት መላእክት፡ በአጠገባቸው ቆመው፡ 'እናንተ፡ የገሊላ ሰዎች ሆይ! ወደሰማይ እየተመለከታችሁ፡ ስለምን ቆማችኋል? ይህ፡ ከእናንተ፡ ወደሰማይ የወጣው ኢየሱስ፡ ወደሰማይ ሲኼድ እንዳያችሁት[፲፯]፡ እንዲሁ ይመጣል!"* በሚለው የመጽሐፍ ቃል፡ የተከፈተው ነው::

በሥርዓቶቹ ፍጻሜ ላይ፡ ቀደም ብለው የተጠቀሱትን የቅዱሳት መጻሕፍትን የምሥራች ቃላት መነሻ በማድረግ፡ ስለሣልስትና ስለአርባ ቀን ምሥጢራት፡ መልካም መልእክትን ያዘለ ትምህርታዊ ስብከት ይሰጣል:: በዚህም መልእክት ውስጥ፡ "ሣልስት" የሚባለው ሦስተኛው የቀብር ዕለት፡ በዕረፍተ ሥጋ ቀድመው ለተለዩን ወገኖቻችን፡ የርደተ መቃብራቸው መራራ ማስታወሻ፥ በሕይወተ ሥጋ ወደኋላ ለቀረነው፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን ደግሞ፡ የኀዘን ማጠናከሪያ ቀን ሳይኾን፡ የእነርሱም፥ የእኛም፡ የኹላችንም ነፍስ፡ በሕይወተ ሥጋ ሣለች፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፡ በኲር ኾኗት፡ የመጀመሪያውን የመንፈስ ትንሣኤ ዕድል አግኝታ፡ በምድር ላይ፡ በተድላ ገነት የቆየችና የምትቆይ መኾኗን፥ አኹን፡ በእነርሱ፡ እውን ኾኖ እንደተፈጸመው ኹሉ፡ የጽዋ ተራዋ ደርሶ፡ ወደሕይወተ ነፍስ በተሸጋገረችበትና በምትሸጋገርበት ጊዜም፡ ይህንኑ፡ የቆየችበትን ህልውናዋን፡ የምትቀጥል መኾኗን፥ በመጨረሻም፡ ኹላችንም ተገናኝተንና በአንድነት ኾነን፡ ዘላለማዊዉን የሕይወት ልዕልና ለመቀዳጀት፡ የትንሣኤ ዘጉባዔ አዋጅ ሲሰማ፡ በአዲሱ የትንሣኤ አካል የምትነሣ መኾኗን የምናረጋግጥበት ዕለት መኾኑ በሰፊው ይብራራል::

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን።
### ትክክለኛው የኢትዮጵያውያን የሣልስትና የአርባ ቀን ሥርዓት።

---

*ጥያቄ፦ የሰው ነፍስ፡ ከሥጋዋ በምትለይበት ጊዜ የሚደርሰው ኹኔታና ከተለየች በኋላ፡ የሚኖራት ህልውና፡ "ምን ዓይነት ይኾን?" የሚለው ጥያቄ፡ ሰብአዊዉን ፍጡር፡ ሲያስጨንቅ የኖረ ነውና፤ በሃይማኖታችንም፡ ይኸው ጥያቄ፡ መልስ እንደተሰጠበት ስለምናምን፡ ይህንኑ፡ ለእኛ ብጤዎች የተሠወረውን ምሥጢር፡ እዚህ ላይ ገላልጸህ ብትነግረን?*

መልስ፦ አዎን! የሰው ነፍስ፡ ከሥጋዋ በምትለይበት ጊዜ ስለሚደርሰው ኹኔታና ከተለየች በኋላ፡ ስለሚኖራት ህልውና፡ የሰው ልጆች፡ በማመንታትና ግራ በመጋባት፡ ሲጨነቁበት የኖሩና የሚኖሩ መኾናቸው የታወቀ ነው። ይኹን እንጂ፡ ነፍስ፡ ከሥጋዋ እንደተለየች፡ ስለሚኖራት ህልውና፡ ያለውን ምሥጢራዊ እውነታ፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና በኢየሱስ ክርስቶስ፡ "ክርስቲያን" የተባሉት ጭምር፡ አኹን፡ በሕይወተ ሥጋ እያለን፡ አስቀድመን፡ በሃይማኖትና በመንፈሳዊው አእምሮአችን አውቀነውና ተዘጋጅተንበት ልንቆይ ስለሚገባን፡ እንደሚከተለው እገልጽላችኋለሁ፦

፩ኛ፡ ነፍስ፡ ከሥጋ የመለየቷ ትንግርት፡ "ሞት" ይባላል፤ እርሱንም ፈጣሪ ሳይኾን፡ ራሱ፡ ሰብአዊው ፍጡር፡ በግል ፍላጎቱ፡ መርጦና ወስኖ ያመጣው መኾኑን አውቃችኋል፤ ሰው፡ በዚህ ዓለም፡ እንደገና፡ ከራሱ እያመነጨ ያከማቻቸውን ችግሮቹንና መፍትሔ ያጣላቸውን ጠንቆች ኹሉ፡ በራሱ ለማስወገድ ፈጽሞ እንዳቃተው፡ እርሱ፡ በራሱ ሊፈጽም ያቃተውን ፍላጎቱንም፡ ፈጣሪው፡ በቤዛነቱ አሟልቶ፡ ለድሉ ቢያበቃው፡ ይህን፡ የድል ጸጋ "አልቀበልም!" ብሎ መጽናቱን፡ ይኸው፡ እየራሳችሁ ትመለከታላችሁ።

ስለዚህ፡ ጠንቀኞች ችግሮቹን ኹሉ ለማስወገድ፡ በእርሱ በኩል፡ የመጨረሻው ፍቱን ኃይል ኾኖለት ያገኘው፡ ቀደም አድርጎ፡ በገዛ ራሱ ላይ ያመጣው፡ ይኸው "ሞት" ብቻ በመኾኑ፡ "ሞት፡ መድኃኒት ነው!"፡ "ሞት፡ ዕረፍት ነው!" የሚል፡ ቅጥያና የክብር ስሞችን ሰጥቶ ሲያሞካሸው ታያላችሁ።

አዎን! "ሞት"፡ በጥልቅ ስሜት ተውጠን የምንወስድበት፡ የህልውና ምዕራፍና ሽግግር ነው፤ ይህንም እውነታ፡ በየጊዜው፡ ከአጠገባችን በሚለዩን፡ በምንወድዳቸው ወገኖቻችን ላይ በሚደርሰው ኹኔታ እናየዋለን፤ ይህን እውን ድርጊት የምናመሳስለው፡ በሰብእናችን ላይ፡ በየዕለቱ ከሚደርሰውና በፍጹም ዕረፍት ከምንመሰጥበት፡ ከከባዱ የእንቅልፍ መኝታችን ጋር ነው፤ በዚህ መመሳሰል፡ ሞትን፡ ከአንዱ የኑሮ ሥርዓት፡ ወደሌላው የምንሸጋገርበት፡ የሕይወት ድልድያ ኾኖን እናገኘዋለን። ስለዚህ፡ የአሟሟታችንን ነገር የምናስበው፡ ደክሞን፡ ዕረፍት ስንፈልግ፡ ጥሩ እንቅልፍን ለመተኛት፡ አልጋችንን እንደምንናፍቅ አድርገን ሊኾን ይገባል፤ እውነታው፡ ይህ ነውና። "እከሌ አንቀላፋ!" "እንቅልፍ፡ የሞት ታናሽ ወንድም ነው!" የሚባለውም፡ ከዚህ የተነሣ መኾኑን፡ በቀላሉ ትገነዘቡታላችሁ!

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

በሞታችን ጊዜ፡ የነፍሳችን ኹኔታ፡ ምንን እንደሚመስል ላብሥራችሁ?! ያ ኹኔታዋ፡ በእውነተኛ ፍላጎቷ ይገለጣል፡ "ፍላጎቷ" የሚባለውም፡ እጅግ በደከመን ጊዜ፡ በአልጋችን ላይ ወድቀን፡ ጥሩ እንቅልፍን ለመተኛት እንደምንጓጓ፡ ወይም፡ በሕመም የሚሠቃይ ሰው፡ ከዚያ ሥቃዩ የሚያሳርፈውን ፈዋሽ መድኃኒት ለማግኘት እንደሚናፍቅ፡ እርሷም፡ በዚያ፡ በመጨረሻው እንቅልፍና ዕረፍት ለመወሰድ የሚኖራት ጉጉትና ናፍቆት ነው:: ይህን እውነታ ማመኑ፡ የኀሊና ዕረፍትን ይሰጣል::

ይህ ሥጋችን፡ ይህችው ነፍሳችን፡ ለብሳውና በዚህ ዓለም፡ ተገልጣበት፥ ገዝፋም እየታየችበት፥ እየተገለገለችበትና እያገለገለችበት ትኖር ዘንድ፡ ከፈጣሪዋ የተሰጣት ልዩ ልብሷ መኾኑን፡ እርሱንም፡ ነፍሳችን፡ ወደዚያ መሸጋገሪያ እንቅልፏና ዕረፍቷ በምትኼድበት ጊዜ፡ ከመኝታ በፊት፡ ወዲያ፡ አወላልቀን እንደምንጥለው፡ የቀን ልብሳችን፡ አውልቃና ጥላው የምትኼደው መኾኑን አውቃችኋል:: በዚህ ረገድ፡ *"ነፍስ፡ ከመብል፥ ሰውነትም፡ ከልብስ አይበልጥምን?"* ያለውን የጌታን ቃል[፻፳] ታስታውሳላችሁ::

፩ኛ፡ ነፍሳችን፡ በሕይወተ ሥጋ ሣለች፡ ከቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷና ምግባርዋ የተነሣ፡ በመጀመሪያው ትንሣኤ፡ ዕድል ፈንታን አግኝታ፡ በዚህ ዓለም፡ በመንፈሳዊው ትንሣኤ፡ ትኖር እንደነበረ ኹሉ፡ ከሥጋዋ እንደተለየችና ከዚያም በኋላ፡ ይህንኑ፡ የመንፈሳዊ ትንሣኤ ህልውናዋን፡ በበለጠ ነጻነትና ሐሤት ትቀጥላለች::

ይህችው ነፍስ፡ በሥጋ በኖረችበትና በምትወድዳቸው ወገኖቿ ዘንድ፥ ሥጋዋም ባረፈበት ቦታ አካባቢ፡ እንደፈጣሪዋና ጌታዋ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለሦስት መዓልትና ለሦስት ሌሊት፥ ከሣልስቷ በኋላም፡ እስከአርባኛዋ ቀን ድረስ፡ አኹንም፡ እንደፈጣሪዋና ጌታዋ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በምድር አካባቢ፡ ወደምትወድዳቸው ወገኖቿና ወደፈቀደችበት ቦታ ስትዘዋወር ትቆያለች፤ ከሥጋዋ በተለየች፡ በአርባኛዋም ቀን፡ እንደፈጣሪዋና ጌታዋ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወደሰማያዊቷ ማደሪያዋ፡ ወደገነት ፈጽማ ታርጋለች::

፫ኛ፡ ነፍስ፡ ለትንሣኤዋና ለዕርገቷ በኵር በኾነው፡ በእርሱ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤና ዕርገት፡ በዓፀደ ሥጋ ሣለች፡ የመጀመሪያው የመንፈስ ትንሣኤና ዕርገት ባለዕድል ኾና እንደኖረች ኹሉ፡ በዓፀደ ነፍስም፡ ሥጋዋ፡ ወደመቃብር በወረደበት፡ በሣልስቱ ዕለት፡ በቤተ መቅደስ በሚካኼደው ሥርዓተ ጸሎት፡ ከወገኖቿ ጋር ተገኝታ፡ የትንሣኤ በዓሏን ታከብራለች:: በአርባኛውም ቀን፡ እንደሣልስቷ፡ በቤተ መቅደስ በሚካኼደው ሥርዓተ ጸሎት፡ ከወገኖቿ ጋር ተገኝታ፡ የዕርገት በዓሏን ታከብራለች::

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን።
### ትክክለኛው የኢትዮጵያውያን የሣልስትና የአርባ ቀን ሥርዓት።

---

እኛም፡ ነፍሳችን፡ በአካለ መንፈሷ፡ እንዲህ ተነሥታ፡ ወደፈጣሪዋ የምታርግ መኾኗን አምነን፡ በዓፀደ ነፍስ ያሉትንም ኾነ፡ በዓፀደ ሥጋ የምንገኘውን፡ ኹላችንንም፡ ለዚህ ጸጋና ክብር ያበቃንን፡ አምላካችንን ኢየሱስ ክርስቶስንና እርሱን የወለደችልንን፡ ቅድስት እናቱን ድንግል ማርያምን በማመስገን፡ ይህችን የወገናችንን ነፍስ፡ የሣልስት ትንሣኤና የአርባ ቀን ዕርገት፡ በቤተ መቅደሳችን ተሰባስበን፡ በሃይማኖታዊው የትፍሥሕት ስሜት እናከብራለን።

ከሣልስትና ከአርባ ቀኖች መታሰቢያ በቀር፡ ከእነዚህ ጋር በማያያዝ፡ ምእመናንና ምእመናት ወገኖቻችን፡ ካረፉበት ጊዜ ጀምሮ፡ ፯ኛ፡ ፲፪ኛ፡ ፴ኛ፡ ፵ኛ፡ ፹ኛ፡ ሙት ዓመትና ፯ኛ ዓመት፡ በሚባሉት ጊዜያት፡ የመታሰቢያ ጸሎት እናደርግላቸዋለን፡ የዚህም መሠረታዊው ምክንያት፡ በእነርሱና በእኛ መካከል ያለው የማያቋርጠው መንፈሳዊ ግንኙነት፡ ተጠናክሮ የቀጠለ መኾኑን፡ በይፋ ለመግለጽ ነው። የሥርዓቱ ፈለግ ግን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ፡ እስከዕርገቱ ቀን ድረስ፡ ለደቀ መዛሙርቱ እየተገለጸ የታየባቸውን ጊዜያት፡ የጌታን የጥምቀቱን ዓመትና ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አቤሜሌክ የተጠመቀበትን ዕድሜ፡ ወንዶች ምዕመናንና ሴቶች ምዕመናት፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ ልጅነትን፡ ከእግዚአብሔር ያገኙበትን፡ ፵ኛ እና ፹ኛ ቀኖች፡ የዓመቱን መታሰቢያና ሙሉ ሱባዔ የኾነውን፡ ፯ኛውን ዓመት ተከትሎ የሚፈጸም መኾኑን ሊታወቁት ይገባል።

እንግዲህ፡ ወደፊት፡ እናንተ፡ በሕይወተ ሥጋ፡ ወደኋላ ቀሪዎች ኾናችሁ፡ የእናንተ በኾኑት ተቀድማችሁ፡ እየራሳችሁን አግኝታችሁ፡ ጽዋው በሚደርሳችሁ ጊዜ፡ ይህን የመሰለውን ሥርዓተ ጸሎት፡ በአርአያነት ተከትላችሁ፡ የሣልስትና የአርባ ልቅሶአችሁን፡ የቀሩትንም የመታሰቢያ ዕለታት፡ በትንሣኤና በዕርገት ፍሥሓችሁ አስተካክላችሁና ተክታችሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በተቀዳጃችሁት ጸጋ፡ ባማረና በሚያስደስት ሃይማኖታዊ ሥርዓት ልትፈጽሙት ይገባችኋል።

#### ከትንሣኤ በኋላ ስላለው ህልውናችን።

ጥያቄ፡- *በዕረፍተ ሥጋ ለተለዩንና ለሚለዩን ወገኖቻችን፡ ለእየራሳችንም፡ በሣልስትና በአርባ ቀኖቻችን፡ ከዚያም በኋላ ባሉት የመታሰቢያ ዕለታት፡ ስለሚፈጸመው ትክክለኛ ሥርዓታችን፡ ይህን ያህልካስረዳኸን፡ አኹን ደግሞ፡ ከትንሣኤ በኋላ ያለው ህልውናችን፡ ምንን እንደሚመስል፡ እውን አድርገህ ብታሳየን?*

መልስ፡- ከትንሣኤ በኋላ ያለው ህልውና፡ ለክፉዎችም፡ ለደጎችም፡ ዛሬ፡ በዚህ ዓለም፡ በሥጋ ከሚኖሩት፡ እጅግ የተለየ ነው፤ ይህንኑም፡ ቀደም ብለው የተጠቀሱትንና ያልተጠቀሱትን የእግዚአብሔር ቃላት መሠረት በማድረግ፡ እንደሚከተለው፡ ማሳየት ይቻላል፡-

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፣

## “ፈጣሪዬ” የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ይኸውም፡ በአንድ በኩል፡ የክፉው ዲያብሎስ ወገኖች የኾኑት ኃጥኣን፡ ወይም፡ ሓሰተኞች፡ የሥጋና የነፍስ ፈቃዳቸው፡ ክፋት፥ ኃጢኣትና ሞት በሠለጠኑበት ህልውና ውስጥ ኾነው፡ ከእነዚሁ የሚመነጭ ፍላጎታቸውን እያረኩ መኖርን የሚሹ ቢመኾናቸው፡ ከትንሣኤ በኋላ ያለው ህልውናቸው፡ የዚያ ፈቃዳቸውና ፍላጎታቸው ዋጋ በኾነው ጨለማና እሳት፡ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት በጸናበት ዓለም ውስጥ መሠቃየት ነው።

በሌላው በኩል ደግሞ፡ የደጉ እግዚአብሔር ወገኖች የኾኑት ጻድቃን፡ ወይም እውነተኞች፡ የሥጋና የነፍስ ፈቃዳቸው፡ ደግነት፡ ጽድቅና ሕይወት በሠለጠኑበት ህልውና ውስጥ ኾነው፡ ከእነዚሁ የሚመነጭ ፍላጎታቸውን እያረኩ መኖርን የሚሹ በመኾናቸው፡ ከትንሣኤ በኋላ ያለው ህልውናቸው፡ የዚያ ፈቃዳቸውና ፍላጎታቸው ዋጋ በኾነው፡ በማያቋርጥ ብርሃን በደመቀችና በንጹሕ ፈሳሽ ውኃ በለመለመች፥ በማኅሌትና በይባቤ ድምፆችም በተመላች፡ የተድላና ደስታ ዓለም መኖር ነው።

ይህም፡ ዛሬ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እነዚህን ጠንቆች ኹሉ፡ በፈተናውና በሕማማተ መስቀሉ፡ በሞቱና በትንሣኤው አስወግዶ፡ በድል አድራጊነት፡ ከነእናቱ ከነገሠ በኋላ፡ ይህን ድል፡ ለደጎች ጻድቃን ስላጎናጸፋቸው፡ እነርሱም፡ እነሆ፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋ፡ ከእነዚያ ጠንቆች፡ ማለትም፡ ከክፋት፥ ከኃጢኣትና ከሞት ነጻ በኾነው፡ በፊተኛው የመንፈስ ትንሣኤ፡ በምድር ላይ ለመኖር በመቻላቸው ይረጋገጣል። ክፉዎች፡ በዚህ ዓለም፡ ከነአበጋዛቸው ዲያብሎስ፡ በንስሓ የማይመለሱ ኾነው፡ እነሆ ዛሬ፡ የሥጋ ህልውናቸውን፡ በዚያው በመረጡት ሰይጣናዊ መንገድ፡ ቀጥለው ለመኖር በመቻላቸው፡ ተረጋግጦ እንደሚታየው ማለት ነው።

ከትንሣኤ በኋላ ያለው፡ የክፉዎች ህልውናና የደጋጎች ሕይወት ምን እንደሚመስል፡ *“በዓለም መጨረሻም፡ እንዲሁ ይኾናል። የሰው ልጅ፡ መላእክቱን ይልካል፣ ከመንግሥቱም፡ እንቅፋትን ኹሉ፥ ዓመፃ የሚያደርጉትንም ይለቅማሉ፣ ወደእቶን እሳትም ይጥሏቸዋል፣ በዚያ፡ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይኾናል። በዚያን ጊዜ፡ ጻድቃን፡ በአባታቸው መንግሥት፡ እንደፀሓይ ይበራሉ።”* ደግሞም፡ *“ትንሣኤ ሙታንን የሚክዱ፡ ከሰዱቃውያን፡ አንዳንዶቹ፡ ቀርበው፡”* በጠየቁት ጊዜ፡ *“የዚህ ዓለም ልጆች፡ ያገባሉ፥ ይጋባሉም፣ ያን ዓለምና ከሙታን ትንሣኤ ሊያገኙ የሚገባቸው፡ እነዚያ ግን፡ አያገቡም፥ አይጋቡምም፣ እንደመላእክት ናቸውና፡ ሊሞቱም፡ ወደፊት አይቻላቸውም፣ የትንሣኤም ልጆች ስለኾኑ፡ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው።”* ሲል፡ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገራቸው ቃላት ያመለክታሉ።

ከዚህም ጋር፡ በራእየ ዮሓንስ የተጻፈው ቃል፡ ከትንሣኤ ሙታን በኋላ ስላለው የህልውና ዓለም፡ እንዲህ እያለ ያብራራል፦

*“ሺሁም ዓመት ሲፈጸም፡ ሰይጣን፡ ከእሥራቱ ይፈታል፣ በአራቱም፡ በምድር ማዕዘን ያሉትን አሕዛብ፥ ጎግንና ማጎግን እንዲያስታቸው፥ ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል።*

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖ ::
## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን::
## ከትንሣኤ በኋላ ስላለው ህልውናችን::

---

*"የእነዚህም: ቁጥራቸው: እንደባሕር አሸዋ የሚያህል ነው፤ ወደምድር ስፋትም ወጡ፤ የቅዱሳንንም ሠፈርና የተወደደችውን ከተማ ከበቡ:: እሳትም: ከሰማይ: ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዳ በላቻቸው:: ያሳታቸውም ዲያብሎስ: አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ: ወዳሉበት: ወደእሳቱና ወደዲኑ ባሕር ተጣለ፤ በዚያም: ለዘለዓለምም እስከዘለዓለም: ቀንና ሌሊት ይሠቃያሉ::*

*"ታላቅና ነጭ ዙፋንን: በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ: ምድርና ሰማይም: ከፊቱ ሸሹ፤ሥፍራም አልተገኘላቸውም:: ሙታንንም: ታናናሾችንና ታላላቆችን: በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፡ መጻሕፍትም ተከፈቱ፡ ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ፡ እርሱም: የሕይወት መጽሐፍ ነው:: ሙታንም: በመጻሕፍት ተጽፎ እንደነበረ: እንደሥራቸው መጠን ተከፈሉ:: ባሕርም: በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ:: ሞትና ሲኦልም: በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ:: እያንዳንዱም: እንደሥራው መጠን ተከፈለ:: ሞትና ሲኦልም: በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ:: ይህም የእሳት ባሕር: ኹለተኛው ሞት ነው:: በሕይወትም መጽሐፍ: ተጽፎ ያልተገኘ ማንም: በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ::*

*"አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፡ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፤ ባሕርም: ወደፊት የለም:: ቅድስቲቱም ከተማ: አዲሲቱ ኢየሩሳሌም: ለባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ: ተዘጋጅታ: ከሰማይ: ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ:: ታላቅም ድምፅ ከሰማይ:- 'እነሆ : የእግዚአብሔር ድንኳን: በሰዎች መካከል ነው፤ ከእነርሱም ጋር ያድራል፤ እነርሱም: ሕዝቡ ይኾናሉ፤ እግዚአብሔርም: እርሱ ራሱ: ከእነርሱ ጋር ኾኖ: አምላካቸው ይኾናል፤ እንባዎችንም ኹሉ: ከዓይኖቻቸው ያብሳል፤ ሞትም: ከእንግዲህ ወዲህ አይኾንም፤ ኀዘንም ቢኾን: ወይም ጩኸት: ወይም ሥቃይ: ከእንግዲህ ወዲህ አይኾንም፤ የቀደመው ሥርዓት አልፏልና!' ብሎ ሲናገር ሰማሁ::*

*"በዙፋንም የተቀመጠው: 'እነሆ: ኹሉን አዲስ አደርጋለሁ!' አለ:: ...ተፈጽሟል:: አልፋና ኦሜጋ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ! ለተጠማ: ከሕይወት ውኃ ምንጭ: እንዲያው: እኔ እሰጣለሁ:: ድል የሚነሣ: ይህን ይወርሳል፤ አምላክም እኾነዋለሁ፤ እርሱም: ልጅ ይኾነኛል::*

*"ዳሩ ግን: የሚፈሩና የማያምኑ፥ የርኵሳንም፥ የነፍሰ ገዳዮችም፥ የሴሰኞዎችም፥ የአስማተኞዎችም፥ ጣዖትንም የሚያመልኩ፥ የሐሰተኞዎችም ኹሉ: ዕድላቸው: በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው:: ይኸውም: ኹለተኛው ሞት ነው::'"*[፻፱]

### ስለጌታችን ዳግም ምጽአትና ስለዓለሙ ፍጻሜ::

**ጥያቄ:-** *የአምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ: የዳግመኛ ምጽአቱና የዓለሙ ፍጻሜ ነገር እንዴት ነው? ምልክቱና በዚያን ጊዜ የሚኾነውስ: ከቶ ምንድር ነው?*

መልስ:- እስካሁን የተነጋገርንበት፡ የሙታን ትንሣኤ የሚፈጸመው፡ "እግዚአብሔርስ ገሃደ ይመጽእ፡ ወአምላክነ፡ ኢያረምም፡ እሳት ይነድድ ቅድሜሁ::" ማለትም፡ "እግዚአብሔር አምላካችን፡ ዝምታው፡ ትእግሥቱ አብቅቶ፡ እሳት በፊቱ እየነደደ፡ በግልጥ ይመጣል!" የሚለው የነቢያት ቃል ይፈጸም ዘንድ፡ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በግርማ መለኮቱ፡ በገሃድ በሚመጣበት፡ በኹለተኛ ምጽአቱ ጊዜ ነው::

በኢየሩሳሌም፡ ሄሮድስ አሳድሶት የነበረው፡ የሰሎሞን ቤተ መቅደስ፡ ሕንፃው፡ እንዴት ያማረ እንደኾነ፡ ደቀ መዛሙርቱ እያደነቁ፡ ለመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባሳዩት ጊዜ፡ "እውነት እላችኋለሁ! ይህ ኹሉ፡ የምታዩት ሕንፃ፡ ድንጋዩ በድንጋዩ ላይ ወድቆ፡ ሳይፈራርስ አይቀርም!" ስላላቸው፡ ነገሩ ከንክኗቸው፡ "በደብረ ዘይት፡ ለብቻቸው ሳሉ፡ ወደእርሱ ቀርበው፡ 'ንገረን! ይህ መቼ ይኾናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ፡ ምልክቱ ምንድር ነው?'" ብለው ላቀረቡለት ጥያቄ፡ በሰጣቸው ምላሽ ውስጥ፡ ይህ፡ የእናንተም ጥያቄ፡ ተጠቃልሎ ይገኛል:: ይኸውም፡ እርሱ፡ በግልጥ፡ በግርማ መለኮቱ ከመምጣቱና የዓለሙ ፍጻሜ ከመኾኑ በፊት፡ የሚከሠቱ ምልክቶችና መከራዎች መኖራቸውን፡ እነዚያም ምልክቶችና መከራዎች፡ ምን እንደኾኑ፡ ሊያደርጓቸው ከሚገባቸው ጥንቃቄዎች ጋር በመዘርዘር፡ ምሥጢሩን አብራርቶ የገለጸበት ሰፊ ትምህርቱ ነው::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዚህ ትምህርቱ ውስጥ፡ ዳግም ምጽአቱና የዓለሙ መጨረሻ መቃረቡን የሚያሳዩ ምልክቶች፡ አስቀድመው፡ በዓለሙ ኹሉ፡ በየአገሩም እንደሚከሠቱ ነግሮአቸዋል:: ከእነዚህ፡ ሃያ አንድ ያህል ከሚኾኑት፡ ዋና ዋና ምልክቶች መካከል፡ ዛሬ፡ የእርሱ፡ የቃል ኪዳን ሕዝቡ ለኾንነው ኢትዮጵያውያን፡ በአንደኛ፡ የገድል ዕድገት ደረጃ፡ የሚከሠቱት ቀዳሚዎቹ፡ የሚከተሉት ናቸው:-

፩ኛ፡ "እኔ ክርስቶስ ነኝ!" እያሉ፡ በስሙ ሳይቀር የሚነሡትና ብዙዎችን የሚያስቱት፡ ብዙዎች ሐሳውያን መሢሖች (የሐሰት ምሁራን)፡ እንዲሁም፡ "የክርስቶስ መልእክተኞች ነን!" እያሉ የሚመጡትና ብዙዎችንም የሚያስቱት ብዙዎች፡ ሐሳውያን ነቢያት (የሐሰት ሊቃውንት፥ መምህራን፡ ሰባክያንና ባሕታውያን)፥

፪ኛ፡ ሕዝብ፡ በሕዝብ ላይ፡ መንግሥትም፡ በመንግሥት ላይ፡ በዓመፅ እየተነሣና በየቦታው እየታወጀ፡ የእርስ በርስ ፍጅትንና ዕልቂትን ያስከተለ ጦርነት፥

፫ኛ፡ በያለበት የተስፋፋ ድርቅ፡ ረሃብ እና ችጋር፡

፬ኛ፡ በዓለም ኅብረተሰብ መካከል የሰፈነ ቀሣፊ በሽታ የኾነ ቸነፈር፡

፭ኛ፡ በልዩ ልዩ ሥፍራ መድረሱ የቀጠለ፡ የምድር መናወጥ:: እነዚህም ኹሉ፡ የምጥ ጣር መጀመሪያ ስለኾኑ፡ ይህም ኹሉ ሊኾን ግድ ስለኾነ፡ መጨረሻውም፡ ገና ስለኾነ፡ ማንም እንዳያስታቸው እንዲጠነቀቁ፡ በሃይማኖታቸው ጸንተውና ተጠብቀው እንዲገኙ እንጂ፡ እንዳይደነግጡ አጠንክሮ አሳስቧቸዋል::

# ምዕራፍ ፫፡ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት፡፡
## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን፡፡
### ስለጌታችን ዳግም ምጽአትና ስለዓለሙ ፍጻሜ፡፡

---

ከቀዳሚዎቹ ቀጥለው፡ በኹለተኛው፡ የገድል ዕድገት ደረጃ የሚከሠቱት፡ ጽኑ ምልክቶች ደግሞ፡ የሚከተሉት መኾናቸውን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስታውቋቸዋል፡ እነርሱም፡-

፮ኛ፡ የእርሱ፡ የቃል ኪዳን ወገኖቹና በስሙ የተጠሩ በመኾናቸው ምክንያት ብቻ፡ ኢትዮጵያውያኑ፡ ከቅዱሱ ኪዳን አምላካቸው ተቃዋሚዎች፡ የጠላትነት በቀልን፡ በብርቱ ጥላቻ፡ ያለማቋረጥ እየተቀበሉ፡ *መሰደዳቸው፡ ለመከራ አልፈው መሰጠታቸውና መገደላቸው፡*

*፯ኛ፡ ከዚህ ኹሉ ጽኑ መከራ የተነሣ፡ ሰዎች ወደክህደት፡ ዓመፅና ምንዝርና ኀጢአት ስለሚያዘነብሉ፡ ከቀሩት ኢትዮጵያውያን መካከል ሳይቀር፡ በብዙዎች ዘንድ፡ የፍቅር መቀዝቀዝና መሰንከል ደርሶ፡ የእርስ በርስ አሳልፎ መሰጣጣትና መጣላት፡*

*፰ኛ፡ ለአሕዛብም ኹሉ ምስክር እንዲኾን፡ ይህ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የምሥራች ቃል፡ በዓለም ኹሉ መሰበኩ ናቸው፡፡*

ይህ ስምንተኛው ምልክት፡ ለዓለሙ ፍጻሜና ለእርሱ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት መድረስ፡ ማረጋገጫ መኾኑን ገልጿላቸዋል፡፡

ከዚህ በኋላ፡ በዚሁ፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት መሠረት፡ በሦስተኛው፡ የገድል ዕድገት ደረጃ የሚከሠቱት ታላላቅ ምልክቶች፡ የሚከተሉት መኾናቸውን፡ አከታትሎ ዘርዝሮላቸዋል፤ እነርሱም፡-

*፱ኛ፡ በነቢዩ በዳንኤል ትንቢት፡ "የጥፋት ርኵሰት" የተባለው* ዲያብሎስ፡ በወኪሎቹ አለቆች አማካይነት፡ *በተቀደሰችው ሥፍራ፡* በኢትዮጵያ ብቻ ሳይኾን፥ በዓለም ደረጃ ጭምር፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው መንበሮች ላይ *ተገልጦና ቆሞ መታየቱ፥*

*፲ኛ፡ በዚያን ጊዜ የሚደርሰው፡ ከዓለም መጀመሪያ አንሥቶ፡ እስከዛሬ ድረስ ያልኾነውና እንግዲህም ከቶ የማይኾነው ታላቅ መከራ፡*

*፲፩ኛ፡ ሐሳውያን መሢሖችና ሐሰተኞች የሃይማኖት መሪዎች፡ ከኢትዮጵያውያን መካከል፡ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ፡ የሚያሳዩዋቸው፡ የኀይል ምልክቶች ናቸው፡፡*

በዚህ፡ የመከራ ዘመን፡ ሊፈጽሙት ስለሚገባቸው የሃይማኖት ጽናትና የምግባር ጥንቃቄ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለቃል ኪዳን ወገኖቹ ምእመናን የሰጠው *መመሪያ* አለ፡ ይኸውም፡ *መከራው ሲጀምር፡ በሜዳ ያሉት፡ ወደተራራዎች እንዲሸሹ፡ በሰገነትም ያለ፡ በቤቱ ያለውን ሊወስድ፡ እንዳይወርድ፡ በእርሻም ያለ፡ ልብሱን ይወስድ ዘንድ፡ ወደኋላው እንዳይመለስ* ካስጠነቀቀ በኋላ፡ *"በዚያች ወራት፡ ለርጉዞችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው! ነገር ግን፡ ሽሽታችሁ፡ በክረምት፡ ወይም በሰንበት እንዳይኾን፡ ጸልዩ!"* የሚለው መመሪያው ነው፡፡

## ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
### "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

፲፪ኛ፡ "ይህን መመሪያውን ሰጥቶ፡ ብዙ ቀኖችም ሳይቆይ፡ ተቃዋሚዎቹ፡ እርሱን ሊሰቅሉት፡ መስቀሉን አሸክመው፡ ወደቀራንዮ በሚወስዱት ጊዜ፡ "ዋይ! ዋይ!" ከሚሉና ሙሾ ከሚያወጡ ሴቶችና ከሕዝቡ፡ እጅግ ብዙዎች፡ ተከትለውት አየና፡ ወደእነርሱ ዞሮ ብሎ፡ "እናንት፡ የኢየሩሳሌም ልጆች! ለእኔስ፡ አታልቅሱልኝ! ዳሩ ግን፡ 'መካኖችና ያልወለዱ ማሕፀኖች፡ ያላጠቡም ጡቶች፡ ብፁዓን ናቸው!' የሚሉበት ጊዜ፡ እነሆ ይመጣል፡ ስለዚህ፡ ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ አልቅሱ! በዚያን ጊዜ፡ ተራራዎችን፡ 'በላያችን ውደቁ!' ኮረብቶችንም፡ 'ሠውሩን!' ይሉ ዘንድ ይጀምራሉ።" ሲል የተናገረው ቃሉ የሚፈጸመው፡ በዚህ የመከራ ዘመን መኾኑን በሃይማኖት ማስተዋልና በመንፈሳዊ ተዘክሮ ልትመለከቱት ያስፈልጋችኋል።

ከዚሁ መመሪያው ጋር አያይዞ፡ ታላቁ መምህራችን፡ እንዲህ ሲል የተናገረውንም ስሙ:-

፲፫ኛ፡ ማንም፡ 'እነሆ፡ ክርስቶስ፡ ከዚህ አለ፡ ማለትም፡ በከተማ፡ በእልፍኝ ውስጥ ተቀምጦ ያስተምራል! ወይም፡ ከዚያ አለ፡ ማለትም፡ በገጠር፡ በበረሀ እየተዘዋወረ ያስተምራል!' ቢላችሁ፡ አትመኑ! አትውጡ! በዚያን ጊዜ፡ የሰው ልጅ (የኢየሱስ ክርስቶስ) አመጣጥ፡ መብረቅ፡ ከምሥራቅ ወጥቶ፡ እስከምዕራብ፡ ለኹሉ እንደሚታይ፡ እንደዚያ፡ በገሃድ ነውና። በድን ወዳለበት፡ በዚያ፡ አሞራዎች እንደሚሰበሰቡ፡ የእርሱ የኾኑትንም፡ እንዲሁ ይሰበስባቸዋልና። "እነሆ፡ አስቀድሜ፡ ኹሉን ነገርኋችሁ!" በማለት፡ መመሪያውን ካብራራላቸው በኋላ፡ "እነዚያ የመከራ ቀኖችስ ባያጥሩ ኖሮ፡ ሥጋ የለበሰ ኹሉ፡ ባልዳነ ነበር፤ ነገር ግን፡ ስለተመረጡት ሰዎች፡ እነዚያ ቀኖች ያጥራሉ።" ሲል፡ የሚያጽናና ቃሉን ተቶላቸዋል።

ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዚህ ትምህርቱ፡ የመምጣቱንና የዓለሙን ፍጻሜ ምልክቶች፡ በዚህ አባበቃም፡ በምሳሌዎች ጭምር አጠናክሮላቸዋል። እነዚህም:-

፲፬ኛ፡ "ምሳሌውንም፡ ከበለስ ተማሩ! የዚች የበለስ ዛፍ፡ ጫፍዋ ሲለሰልስ፡ ቅጠልዋም ሲያቈጠቍጥ፡ (የክረምቱ፡ ማለትም፡ እንደአገራቸው፡ የትፈጥሮ ሥርዓት፡ የዛፉ ቅጠል ኹሉ የሚረግፍበት፡ የቅዝቃዜውና የበረዶው ወራት አብቅቶ፡ ጥቢ ሲኾን፡) ያን ጊዜ፡ በጋ እንደቀረበ ታውቃላችሁ፤ እንዲሁ፡ እናንተ ደግሞ፡ ይህን ኹሉ ሲታዩ፡" ማለትም፡ በበለስ የምትመሰለው፡ "እስራኤል"፡ አገር፥ ሕዝብና መንግሥት ኾና፡ እንደገና ስትቋቋም፡ የሰው ልጅ መምጫውና የዓለሙ ፍጻሜ፡ 'በደጅ እንደቀረበ፡ እወቁ!"

፲፭ኛ፡ "የኖኅ ዘመን እንደነበረ፡ የሰው ልጅ መምጣት፡ እንዲሁ ይኾናልና። በዚያች ወራት፡ ከጥፋት ውኃ በፊት፡ ኖኅ፡ ወደመርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ፡ በዘመኑ የነበሩት ሰዎች፡ ሲበሉና ሲጠጡ፥ ሲያገቡና ሲጋቡ እንደነበሩ፡ የጥፋት ውኃም መጥቶ፡ ኹሉን እስከወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፡ የሰው ልጅ (ኢየሱስ ክርስቶስ) መምጣት ደግሞ፡ እንዲሁ ይኾናል።

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::

## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን::

### ስለጌታችን ዳግም ምጽአትና ስለዓለሙ ፍጻሜ::

---

፲፮ኛ: *"በዚያን ጊዜ: ኹለት ሰዎች: በእርሻ ይኾናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል: አንዱም ይቀራል፤ ኹለት ሴቶች: በወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱ ትወሰዳለች: አንዲቱም ትቀራለች:: ጌታችሁ: በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና: እንግዴህ ንቁ! ያን ግን እወቁ! ባለቤት: ከሌሊቱ: በየትኛው ክፍል: ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ: በነቃ: ቤቱም: እንዲቆፈር: ባልተወውም ነበር:: ስለዚህ: እናንተ ደግሞ: ተዘጋጅታችሁ ኑሩ! የሰው ልጅ: በማታስቡበት ሰዓት: ይመጣልና::"*

፲፯ኛ: በዚያን ጊዜ: እናንተ: *"ምግባቸውን: በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ: ጌታው: በቤተሰቦቹ ላይ የሾመውን ታማኝና ልባም አገልጋይ መስላችሁ ተገኙ! ጌታው መጥቶ: እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው: ያ አገልጋይ: ብፁዕ ነው፤ እውነት እላችኋለሁ! ባለው ኹሉ ላይ ይሾመዋል:: ያ: ክፉ አገልጋይ ግን: 'ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል፣' ብሎ: በልቡ ቢያስብ፥ ባልንጀሮቹን አገልጋዮች: ሊመታ ቢጀምር: ከሰካሮችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ የዚያ አገልጋይ ጌታ: ባልጠበቃት ቀን: ባላወቃትም ሰዓት ይመጣል: ከኹለትም ይሠነጥቀዋል፤ ዕድሉንም: ከግብዞች ጋር ያደርግበታል:: በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይኾናል::*

፲፰ኛ: *"ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት: ግን: ከአባት ብቻ በቀር: የሰማይ መላእክትም ቢኾኑ: ልጅም ቢኾን: የሚያውቅ የለም::* የሚሉት ናቸው::

*"ከዚያች የመከራ ዘመን በኋላም:"* የሚታዩት ምልክቶች ለሥጋውያንና ዓለማውያን ወገኖች: እጅግ አስፈሪና አስደንጋጭ መኾናቸውን: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: ለደቀ መዛሙርቱ ገልጾላቸዋል፤ እነርሱም:-

፲፱ኛ: *ወዲያው የሚደርሱት: የፀሐይ: መጨለምና የጨረቃ ብርሃን መጥፋት፥ የከዋክብት: ከሰማይ መርገፍና የሰማይ ኃይላትም መናወጥ፥*

፳ኛ: ቀጥሎ: *"በዚያኑ ጊዜ የሚኾነው: የሰው ልጅ ምልክት: በሰማይ መታየት: የምድር ወገኖች ኹሉ: እርሱን: በኃይልና በብዙ ክብር: በሰማይ ደመና ሲመጣ ሲያዩት: 'ዋይ! ዋይ!' እያሉ ዋይታን ማሰማት ናቸው ::*

፳፩ኛ: ከዚህ ኹሉ በኋላ: ገበሬ: የደከመበትን የዘሩን ፍሬ: ከአውድማው ሰብስቦ: ወደጎተራው እንደሚከትት: እግዚአብሔርም: *"መላእክቱን: ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፤ ከሰማያትም ዳርቻ: እስከዳርቻው: ከአራቱ ነፋሳት: ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ::"*

እንግዲህ: *"በድን ባለበት: በዚያ: አሞራዎች ይሰበሰባሉ!"* ያለው ምሳሌው: በትርጉም ብቻ ሳይኾን: በግብር: እውን የሚኾንበት: "ትንሣኤ ዘጉባኤ" የተባለው: የመጨረሻው: የሙታን ትንሣኤ: በዚያን ጊዜ ይፈጸማል:: ያም ጊዜ: "የእግዚአብሔር ቀን" የሚባለው ነው::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

አዎን! "ሙታንና ሕያዋን"፡ ተብለው፡ በኹለት የተከፈሉት የሰው ልጆች፡ እንደየፍላጎታቸው ሊቀበሉ የመረጡትን የመጨረሻ ፍርድ ሊያውጅ፡ ፈጣሪና አምላክ፥ ቤዛና መድኀኒት፥ ካህንና ንጉሥ የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዚያ፡ "የእግዚአብሔር ቀን"፡ በግርማ መለኮቱና በክብረ መንግሥቱ ይመጣል።

ያ ቀን፡ ምን እንደሚመስል፥ ምንስ እንደሚካኼድበት፥ ምን ዓይነት ትንግርትም እንደሚታይበት፡ ራሱ፡ የቀኑ ጌታ፡ እስከመጨረሻው ላመኑበት ኹሉ፥ የቃል ኪዳን ልጆቹ ለኾኑት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ በየጾታቸው፡ በምሳሌ አግዝፎ ባስተማራቸው፡ ትምህርቶቹ ገልጾታል፦

ለሴቶቹ፡ እንዲህ ሲል ያስቀድማል፦ *"በዚያን ጊዜ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ መብራታቸውን ይዘው፡ ሙሽራውን* (ኢየሱስ ክርስቶስን) *ሊቀበሉ የወጡ፡ ዐሥር ቈነጃጅትን ትመስላለች። ከእነርሱም፡ አምስቱ ሰነፎች ('ሙታን' የተባሉት፡ ሓሰተኞቹ ኃጥአን)፥ አምስቱም፡ ልባሞች ('ሕያዋን' የተባሉት፡ እውነተኞቹ ጻድቃን) ነበሩ።*

*"ሰነፎቹ፡ መብራታቸውን ይዘው፡ ከእነርሱ ጋር ዘይት ሳይዙ ቀሩ፥ ልባሞቹ ግን፡ ከመብራታቸው ጋር፡ በማሰሮአቸው፡ ዘይታቸውን ያዙ። ሙሽራው በዘገየ ጊዜ፡ ኹሉም፡ እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ተኙ። እኩለ ሌሊት ሲኾን፡ 'እነሆ፡ ሙሽራው መጥቷልና፡ ትቀበሉት ዘንድ ውጡ!' የሚል ሁካታ ኾነ። በዚያን ጊዜ፡ እነዚያ ቈነጃጅት፡ ኹሉም ተነሡና፡ መብራታቸውን አዘጋጁ። ሰነፎቹም፡ ልባሞቹን፡ 'መብራታችን ሊጠፋብን ነው፥ ከዘይታችሁ ስጡን!' አሏቸው። ልባሞቹ ግን፡ መልሰው፡ 'ምናልባት፡ ለእኛና ለእናንተ ባይበቃስ! ይልቅስ፡ ወደሚሸጡት ኼዳችሁ፡ ለራሳችሁ ግዙ!' አሏቸው። ሰነፎቹም ሊገዙ በኼዱ ጊዜ፡ ሙሽራው መጣ። ተዘጋጅተው የነበሩት ልባሞቹ ቈነጃጅት፡ ከእርሱ ጋር ወደሠርጉ ገቡ፤ ደጁም ተዘጋ። በኋላም ደግሞ፡ የቀሩቱ፡ ሰነፎቹ ቈነጃጅት መጡና፡ 'ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! ክፈትልን አሉ። እርሱ ግን፡ መልሶ፡ 'እውነት እላችኋለሁ፤ አላውቃችሁም!' አለ። ስለዚህ፡* (የመምጫዬን) *ቀኒቱንና ሰዓቲቱን አታውቁምና፡ እንግዴህ ንቁ!"*

ለወንዶቹ ደግሞ፡ እንዲህ ሲል ያስከትላል፦ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በይፋ በምትገለጽበት፡ በዚያን ጊዜ፡ *"አገልጋዮቹን ጠርቶ፡ ያለውን ገንዘብ፡ እንደየዓቅማቸው፡ ለአንዱ አምስት፥ ለአንዱ፡ ኹለት፥ ለአንዱም፡ አንድ መክሊት ሰጥቷቸው፡ ወደሌላ አገር ኼዶ፡ ለብዙ ዘመን ከኖረ በኋላ፡ ተመልሶ፡ ምን እንደሠሩበትና ምንስ ያህል እንዳተረፉ እንደተቈጣጠራቸው ባለቤት፡ እንዲሁ ይኾናል።*

*"አምስት መክሊት የተቀበለው፡ ሠርቶበት፡ ሌላ አምስት አትርፎ ኖሮ፡ ለጌታው፡ ዐሥር መክሊትን፥ ያም፡ ኹለት የተቀበለው፡ ሠርቶበት፡ ሌላ ኹለት አትርፎ ኖሮ፡ ለጌታው፡ አራት መክሊትን አቀረቡ፤ እያንዳንዳቸውም፡ 'መልካም! አንተ፡ በጎና ታማኝ አገልጋይ! በጥቂቱ ታምነሃል፤ በብዙ እሾምሃለሁ! ወደጌታህ ደስታ ግባ!' ተብለውና ተሞግሰው፡ በዓል አደረጉ።*

## ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
### ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን።
### ስለጌታችን ዳግም ምጽአትና ስለዓለሙ ፍጻሜ።

---

*"ያ፡ አንድ መክሊት የተቀበለው አገልጋይ ግን፡ ወደጌታው ቀርቦ፡ 'ጌታ ሆይ! ካልዘራህባት የምታጭድ፥ ካልበተንህባትም የምትሰበስብ፡ ጨካኝ ሰው መኾንህን ስላወቅሁ፡ ፈርቼ፡ መክሊትህን በምድር ቀብሬ አስቀምጬው ነበርና፡ መክሊትህ ይኸውልህ! እንካ!' አለ። ጌታውም፡ 'አንተ፡ ክፉና ሃኬተኛ አገልጋይ! ካልዘራሁባት የማጭድ፥ ካልበተንሁባትም የምሰበስብ፡ ጨካኝ ሰው መኾኔን ካወቅህ፡ ገንዘቤን፡ ለለዋጮች፡ አደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበር፡ እኔም፡ መጥቼ፡ ያለኝን፡ ከነትርፉ እቀበል ነበር። ስለዚህ፡ መክሊቱን ውሰዱበት! በሥር መክሊት ላለውም ስጡት! ላለው ኹሉ ይሰጠዋልና፡ ይበዛለትማል፤ ከሌለው ግን፡ ያው፡ ያለው እንኳ ይወሰድበታል። ያን፡ የማይጠቅመውን አገልጋይም፡ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት፡ በውጭ ወዳለው፡ ጨለማ አውጡት!' ብሎ ፈረደበት።"*

በመጨረሻ፡ ለወንዶቹም፥ ለሴቶቹም፡ እንዲህ ሲል ይደመድማል፡- በትስብእቱ፥ በፈተናውና በሕማማተ መስቀሉ፡ ለዘለዓለማዊው ሕይወት ወደበቃንበት ልዕልና፡ እኛን ሰዎችን፡ ከፍ ያደርገን ዘንድ፡ ራሱን፡ *"የሰው ልጅ" እያለ መጥራትን የመረጠው፡ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እንዲያ፡ በግርማ መለኮቱና በክብረ መንግሥቱ መጥቶ፡ ከእርሱም ጋር፡ ቅዱሳን መላእክቱ ኢጅበውት፡ ለመጨረሻው ፍርድ፡ በዙፋኑ ይቀመጣል። በዚያን ጊዜ፡* በሕይወተ *ሥጋቸውም* ኾነ በሕይወተ ነፍሳቸው፡ ሙታንና ሕያዋን ኾነው የቆዩት፥ እንደየምርጫቸውም፡ ብርሃናዊ፡ ወይም ጽልመታዊ የኾነውን፡ አዲሱን የትንሣኤ አካል ለብሰው፡ ከመቃብር የተነሡትም ኾኑ በቅጽበት የተለወጡት *ሕዝብና አሕዛብ፡ በፊቱ ይሰበሰባሉ። እርሱም፡ እረኛ፡ በጎቹን፡ ከፍየሎች እንደሚለይ፡ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል፤ በ'በጎች' የተመሰሉ፡ ጻድቃንን* (እውነተኞችን)፡ *በቀኙ፥ በ'ፍየሎች' የተመሰሉ፡ ኃጥኣንን* (ሓሰተኞችን) *በግራው ያቆማቸዋል።*

*"ንጉሡም* (ኢየሱስ ክርስቶስ)፡ *በቀኙ ያሉትን፡ እንዲህ ይላቸዋል፡- 'እናንተ የአባቴ ቡሩካን! ኑ! ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ፡ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ!* በእኔ በማመን፡ በተቀበላችሁት ሃይማኖት ጸንታችሁ፡ በጎ ምግባርን አድርጋችሁልኛልና።' ጻድቃንም፡ መልሰው፡ 'መቼ አይተንህ፡ በጎ ምግባር አደረግንልህ?' ይሉታል። ንጉሡም፡ *'እውነት እላችኋለሁ! ከኹሉ ለሚያንሱ፡ ከእነዚህ ወንድሞቼ* እና እኅቶቼ፡ *ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት፡ ለእኔ አደረጋችሁት!' ይላቸዋል።*

*"ንጉሡ ቀጥሎ፡ በግራው ያሉትን ደግሞ፡ ይላቸዋል፡- 'እናንተ ርጉማን! ለሰይጣንና ለመላእክቱ፡ ወደተዘጋጀ፡ ወደዘለዓለም እሳት፡ ከእኔ ኺዱ!* በእኔ በማመን፡ በተቀበላችሁት ሃይማኖት ጸንታችሁ፡ በጎ ምግባርን አላደረጋችሁልኝምና።' ኃጥኣንም፡ መልሰው፡ 'መቼ አይተንህ፡ በጎ ምግባር ሳናደርግልህ ቀረን?' ይሉታል። ንጉሡም መልሶ፡ *'እውነት እላችኋለሁ! ከኹሉ ለሚያንሱ፡ ከእነዚህ ወንድሞቼ* እና እኅቶቼ፡ *ለአንዱ እንኳ ስላላደረጋችሁት፡ ለእኔ አላደረጋችሁትም!' ብሎ ይመልስላቸዋል።*

*"ኃጥኣን፡ እንዲህ፡ ወደዘለዓለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን፡ ወደዘለዓለም ሕይወት ይኼዳሉ።"*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፥
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ጥያቄ:- *እንዴ! ቆይ እስኪ! ምን ማለትህ ነው? እዚህ ላይ፡ ሊታብራራልን የሚያስፈልግ፡ አንድ ቁም ነገር አለ፡ ይኸውም፡ "በመጨረሻው ፍርድ ላይ፡ ለሰው፡ ከፈጣሪ የሚቀርብለት ጥያቄ፡ ምግባርን የሚመለከተው ብቻ እንጂ፡ ሃይማኖትን የሚመለከተው አይደለም!" ማለትህ ነውን?!*

መልስ:- አዎን! ይህንማ፡ እናንተም፡ ልታውቁት፡ ሌላውም ኹሉ፡ ሊያውቀው የሚገባ እውነት ነው:: ጥያቄውን፡ ማቅረባችሁ ግን፡ እንደተለመደው አስደንቆኛል፡ አስደስቶኛልም፡ ውይይታችንን፡ በእናንተ በኩል፡ በምን ዓይነት ጥልቅ ፍላጎትና ትኩረት፡ ጥንቃቄም እንደምትከታተሉት፡ ይኸው ጥያቄያችሁ፡ እንደገና እያሳየኝ ነውና::

እውነት ነው፡ ፍጡር ኾኖ፡ ሃይማኖት የሌለው የለም፡ ይህንም፡ "እኔ የምለው እኔነቴ ማነው?" በሚለው፡ በመጀመሪያው ውይይታችን ጊዜ፡ በሚበቃ ተነጋግረንበት አውቃችሁታል፡ "ሃይማኖት"፡ የፈጣሪን መኖርና የራስን ፍጡርነት በማወቅ ላይ የተመሠረተ ስለኾነ፡ ይህም እውነታ፡ በፍጡር ልቦና ውስጥ፡ በተፈጥሮ ተቀርጾ ስለሚገኝ፡ "ሃይማኖት" የሌለው ፍጡር አለመኖሩ፡ በዚህ ይረጋገጣል፡ *"እግዚአብሔር፡ አንድ እንደኾነ፡ አንተ ታምናለህ፡ መልካም ታደርጋለህ፡ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ፡ ይንቀጠቀጡማል::"* ሲል፡ ሐዋርያው የጻፈው፡ ስለዚህ መኾኑን፡ ትገነዘቡታላችሁ::

እንግዲህ፡ ይህን ጥያቄያችሁን በሚመለከት፡ በብርቱ ማስተዋል ያለባችሁን ቁም ነገር ላመልክታችሁ! ይህም፡ በመጨረሻው፡ ዘለዓለማዊ፥ ሰማያዊና ነፍሳዊ የፍርድ አደባባይ ላይ፡ የሚነሣው ርእሰ ጉዳይ፡ <u>ሃይማኖት ሳይኾን፡ ምግባር መኾኑን፤</u> የሚቀርበውም መለኮታዊ ጥያቄ፡ "ለምን አላመናችሁብኝም?" ወይም፡ "እምነታችሁ ምንድር ነው?" የሚል፡ የሃይማኖት ነገር ሳይኾን፡ "ለምን፡ ይህን አደረጋችሁልኝ?" ወይም፡ "ለምን፡ እንዲህ አደረጋችሁብኝም?" የሚል፡ የምግባር ነገር መኾኑን ነው:: ይህ እውነታ፡ እንኳንስ፡ በመለኮት አደባባይ፡ በዚህ፡ በዛሬው፡ ጊዜያዊ፡ ምድራዊና ሥጋዊ ችሎት ላይ ጭምር፡ በዕድሜያችን ደርሶ ስለታየና ስለሚታይ፡ አያስገርምም::

በዚያ፡ በመጨረሻው፡ የፍርድ ጊዜ፡ ፈጣሪ፡ ለዳኝነት የሚቀመጠው፡ "አምነንብሃል!" ብለውት፡ ያን ሃይማኖታቸውን በሥራ በፈጸሙትና ሳይፈጽሙ በቀሩት ላይ ብያኔውን ለማሰማት እንጂ፡ በማያምኑበት ወገኖች ላይ ለመፍረድ አይደለም:: እነዚያማ ያላመኑበት ዲያብሎስና ሠራዊቱ፡ አጋንንት፡ ሰይጣናትና ርኩሳን መናፍስት ኹሉ፡ ደግሞም፡ ከእነዚህ የባሱት፡ ፈጣሪያቸውን ክደው፡ በዲያብሎስ ያመኑት ሰብአውያን ፍጡሮች፡ በዚሁ አቅዋማቸው ምክንያት፡ አስቀድመው፡ እየራሳቸው፡ በእየራሳቸው ላይ፡ ፍርዱን ስለሰጡ፡ ለመለኮታዊው ፍርድ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዙፋን እንዲቀርቡ አያስፈልጋቸውም::

# ምዕራፍ ፫፥ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።
## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን።
### ስለጌታችን ጻግም ምጽአትና ስለዓለሙ ፍጻሜ።

---

*"እናንተ ርጉማን፡ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀ፡ ወደዘለዓለም እሳት ሂዱ!"* የሚባሉት፡ "አምነንብሃል!" ብለውት፡ *ያን ሃይማኖታቸውን፡* በምግባር ሳይፈጽሙ፡ ማለትም፡ በሥራ ላይ አውለው፡ ለመልካም ፍሬ፡ ሌላው ቢቀር እንኳ፡ ለንስሓ ፍሬ ሊያበቁት ያልቻሉት መኾናቸውን፡ ይህ፡ የወንጌላዊው ቃል፡ አረጋግጠ ያሳያል። ደግሞ፡ *"የሳታቸው ዲያብሎስም፡ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት፡ ወደእሳቱና ወደዲኑ ባሕር ተጣለ።"* የሚለው፡ የባለራእዩ ቃል፡ ለዚህ እውነታ፡ በቀ ማስረጃ ኾኖ ይጠቀሳል።

*ፈጣሪ፡* ፍጡሩን፡ በኃላፊነት የሚጠይቀው፡ የሚፈርድለት ወይም የሚፈርድበት፡ ስለአገልግሎቱም፡ በታማኝነት፡ ወይም በከሃዲነት ሥራው፡ ተገቢውን ዋጋ የሚከፍለው እኮ፡ ያ ፍጡር፡ በፈቃደኛነት፡ የፈጣሪውን ህልውና አውቆ፡ በእግዚአብሔርነቱ ያመነበት ሃይማኖት ሲኖረው ብቻ መኾኑን፡ በታላቁ መምህር የምሳሌ ትምህርቶች ውስጥ የተነገረው አረጋግጦታል።

ስለዚህ፡ "ሃይማኖት ብቻ እንጂ፡ ምግባር አያስፈልግም!" የሚለው ትምህርት፡ ከእግዚአብሔር አለመኾኑን፡ በዚህ ተገንዝባችሁ፡ "ሃይማኖት፡ ያለምግባር፡ ምግባር፡ ያለሃይማኖት፡ ነፍስ እንደተለየችው በድን ነው!" በሚለው፡ ኢትዮጵያዊ *መመሪያ* ጸንታችሁ *መኖር* እንዳለባችሁ፡ እዚህ ላይ በአጽንዖት ላሳስባችሁ እወድዳለሁ።

በመደምደሚያው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"እውነት እላችኋለሁ! ይህ ኹሉ እስኪኾን ድረስ፡ ይህ ትውልድ አያልፍም። ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ይህ ቃሌ ግን አያልፍም።"* ስላለ፡ እናንተና እኔ፡ እኛን የመሰሉት ወገኖቻችንም ኹሉ፡ ከመጨረሻው ጥፋት እንድን ዘንድ፡ ይህን ቃሉን፡ እንደኖኅ፡ ልናምነው ይገባናል፡ በኖኅ ዘመን እንደነበረው ትውልድ፡ እንዳንጠፋ፡ ልንጠራጠረው አይገባም። ሰው ኾኖ ያዳነን ፈጣሪያችን፡ እስካሁን የተገለጸውን፡ ይህን፡ ሰፊ መመሪያውንም፡ ያጠቃለለው፡ *"እስከመጨረሻው የሚጸና፡ እርሱ ይድናል!"* በሚለው መለኮታዊ ቃሉ ስለኾነ፡ የዚህን ዘመኑ መከራ፡ በትዕግሥት በመቀበል፡ በሃይማኖታችንና በምግባራችን፡ እስከመጨረሻው ጸንተን እንገኝ ዘንድ፡ ልንጠናከር ይገባናል።[፲፲]

## ትንሣኤ ሙታን አስፈላጊ የኾነበት ምክንያት።

ጥያቄ፡- *እስካሁን የሰማነው የእግዚአብሔር ቃል፡ ከአንተም ያገኘነው ተጨማሪ ሐተታና ማብራሪያ፡ ትንሣኤ ሙታን መኖሩን ሊያሳምነን ችሏል። በመሠረቱ ግን፡ ትንሣኤ ሙታን፡ ለምን እንዳስፈለገ፡ ለዚህ፡ በሰዎች አእምሮ ውስጥ ለሚብሰለሰለው ያልተቋረጠ ጥያቄ፡ ማርኪያ የሚኾን መልስ እንዳለህ ብትነግረን? ወይም፡ ባለቤቱ ፈጣሪ የገለጸልህ ምሥጢር ካለ፡ እኛም እናውቀው ዘንድ፡ እዚህ ላይ አያይዘህ ብታክፍለን?*

## ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
### "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

መልስ፡- ሰው፡ በዲያብሎስ ገዢነት ሥር፡ ባርነትን፥ ኃጢአትንና ሞትን፡ በራሱ ላይ ያመጣው፡ በራሱ የክፋት ዝንባሌ ሲኾን፡ ከዚህ፡ ውርደትና ውድቀት፡ እንሥቶና አውጥቶ፡ በቸርነቱ፡ ወደነበረ ክብሩ ሊመልሰው የፈቀደው ደግሞ፡ ያው፡ ፈጥሮ፡ በተድላ ገነት አኑሮት የነበረው እግዚአብሔር ነው:: ለዚህም፡ ቤዛ ያደረገው፡ ራሱን መኾኑን፡ በምሥጢረ ሥጋዌ፡ በምሥጢረ ጥምቀትና በምሥጢረ ቊርባን ጥያቄዎች መልስ ላይ ተረድታችሁታል::

እግዚአብሔር፡ ሰውን፡ ጥንቱኑ፡ በመልኩ ሲፈጥረው፡ ይኸ ፍጡሩ፡ የፈለገውን ለማሰብ፥ ያን አሳቡንም፡ በፈቀደው መንገድ ለመግለጽና የመረጠውንም፡ በወደደው መልክ ለማድረግ የሚችልበትን፡ የፍላጎት፡ የፈቃድና የምርጫ ፍጹም ነጻነትንና የመወሰንን ሙሉ ሥልጣን የሰጠው መኾኑ፡ በዚህ ውይይታችን፡ የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ፡ በየቦታውና በየጋጣሚውም፡ በተሰጡት ሐተታዎች፡ በሚበቃ ተብራርቷል:: ሰው ግን፡ ይህን የመሰለውን የተፈጥሮ ጸጋ፡ ለበጎ ሳይኾን፡ ለክፋው ስላዋለው፡ ፍጻሜው፡ በይበልጥ፡ ጥፋት ኾኗል:: ፈጣሪ፡ ምንም እንኳ፡ የሰው ምርጫ፡ አሁንም፡ ወደክፋው የሚያዘነብል መኾኑን ቢያውቅም፡ ከክፋው ጋር፡ በጎው ጭምር፡ በበለጠ መጠን፡ አብሮ ለምርጫ እንዲቀርብለት ማድረጉን ስለቀጠለበት፡ እግዚአብሔር፡ ለዚህ እልኸኛና አንገተ-ደንዳና ፍጡሩ፡ ያለው ፍቅርና ቸርነት፡ የቱን ያህል የጸናና ምን ያህል የተትረፈረፈ መኾኑን እነሆ፡ እናንተም፡ በቀላሉ ልትገነዘቡት ትችላላችሁ:: ስለዚህ፡ "በእግዚአብሔር መልክ ተፈጠረ!" የተባለው፡ ይኸው ሰው፡ ፈጣሪው ላዘጋጀለት የዘለዓለም ሕይወት ይበቃ ዘንድ፡ ምርጫው፡ ከሞት ዛፍ ፍሬ ይልቅ፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬን ኾኖ፡ ይህንኑ ፍሬ እንዲበላ ሊያደርግ፡ እግዚአብሔር፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕትነት፡ <u>የንስሓንና የቅዱስ ቊርባንን ጸጋ ለምርጫ ያቀረበለት</u> <u>መኾኑን</u>፡ በግልጽ አውቃችኋል::

እንግዲህ፡ እያንዳንዱ ሰው፡ በዚህ ዓለም ሲኖር፡ ደጉን ወይም ክፋውን፡ እውነቱን ወይም ሐሰቱን፥ ማለትም፡ የእግዚአብሔር ወይም የዲያብሎስ የኾነውን፡ ከኹለት አንዱን፡ በፍጹም ነጻነት፡ አውቆ፥ ለይቶና መርጦ ለመከተል፡ ከመለኮት የተሰጠውን ሥልጣን፡ ያለአንዳች ግዳጅ፡ በገዛ ፈቃዱ ተጠቅሞበት ከኖረ በኋላ፡ በሞተ ሥጋ ሲለይ፡ በሕይወተ ሥጋው፡ እምኖበት የኖረውን የህልውና ፍሬ መሰብሰብ፡ ማለትም፡ የሥራ ዋጋውን መክፈል፥ ወይም፡ መቀበል እንዳለበት፡ የሚያጠያይቅ አይመስለኝም::

በተፈጥሮ በተሰጠው፡ በዚህ የመምረጥ ነጻነቱና የመወሰን ሥልጣኑ በመጠቀም፡ በአንድ ወገን፡ "ለእኔ የሚገባኝ፡ እውነትና በጎ የኾነውን፡ ትክክሉንና ተገቢውን ብቻ ማድረግ እንጂ፡ ክፋውን አይደለም፤ በሌላውም ፍጡር ላይ በደልንና ግፍን መፈጸም አይገባኝም!" ብሎ በማመን፡ ይህን እምነቱን፡ በዚህ መልክ፡ በምድር ላይ፡ በሥራ ሲገልጽ የኖረና የሚኖር አለ::

# ምዕራፍ ፫፡ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን።

### ትንሣኤ ሙታን አስፈላጊ የኾነበት ምክንያት።

---

በሌላው ተቃራኒ ወገን ደግሞ፡ "የለም! ለእኔ የሚገባኝ፡ ሐሰትና ጎጂ የኾነውን፡ ክፉውን ማድረግ ብቻ እንጂ፡ እውነትና በጎውን አይደለም፡ በሌላውም ፍጡር ላይ በደልንና ግፍን እፈጽም ዘንድ፡ ትክክልና ተገቢ ነው!" ብሎ አምኖ፡ በዚህ እምነቱ ሲሠራበት የኖረና የሚኖር አለ።

ታዲያ! ለእነዚህ፡ የተለያየ እምነትና ምግባር ላላቸው፡ ኹለት ሰዎች፡ ለእያንዳንዳቸው፡ ትክክለኛና ተገቢ የኾነውን ዋጋቸውን፡ በነፍስ ወከፍ፡ በከፋዩ በኩል፡ መከፈል፡ በእነርሱም በኩል፡ መከፈል አይገባቸውምን? አዎን! ይህማ፡ በእርግጥ፡ የተፈጥሮ ሥርዓት በመኾኑ፡ ከፋዩ አሠሪም፡ ሊከፍላቸው፡ ተቀባዮቹ ሠራዎችም፡ ሊከፈሉ ይገባቸዋል እንጂ።

ስለዚህ፡ ቀደም ብሎ የተጠቀሰውን፡ የንስሓንና የቅዱስ ቍርባንን ታላቅ ጸጋ፡ ለሰው ልጅ ያጎናጸፈው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዘለዓለማዊ መለኮቱ፡ ክህነቱና ምልክናው፡ በመጨረሻው ዳኝነትና ፍርድ፡ ለፍጥረቱ፡ ዘለዓለማዊውን ዋጋ ለማስረከብ፡ እንደገና፡ በገሃድ ሊመጣ፡ ሰዎችም ኹሉ፡ የሥራ ዋጋቸውን፡ እንደየምርጫቸውና እንደየፍላጎታቸው ይከፈላቸው ዘንድ፡ እንደገና ሕያዋን ኾነው ሊነሡና ሊቀርቡ በግድ ያስፈልጋል። የክርስቶስ ዳግም ምጽአትና የሙታን ትንሣኤ ያስፈለገበት ምክንያቱ እንግዲህ፡ ይህ ነው።

አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ገና በሕይወተ ሥጋ እያለ፡ ስለትንሣኤ ሙታን ምሥጢር፡ ለደቀ መዛሙርቱ ይሰጥ በነበረው ትምህርት፡ ይህን እውነታ፡ እንዲህ በሚል ቃሉ ያመለክታቸው ነበር፦ *"ሰው፡ ዓለሙን ኹሉ ቢያተርፍ፡ ነፍሱንም ቢያጐድል፡ ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው፡ ስለነፍሱ ቤዛ፡ ምን ይሰጣል? የሰው ልጅ፡ ከመላእክቱ ጋር፡ በአባቱ ክብር፡ ይመጣ ዘንድ አለውና። በዚያን ጊዜም፡ ለኹሉ፡ እንደየሥራው ያስረክበዋል።"* ይህንም፡ ዮሐንስ በራእዩ፡ *"ይህን ያየሁትና የሰማሁት፡ እኔ ዮሐንስ ነኝ። በሰማሁትና ባየሁትም ጊዜ፡ ይህን ያሳየኝ መልአክ፡ ...ለእኔ፡ 'ዘመኑ ቀርቧልና፡ የዚህን መጽሐፍ፡ የትንቢት ቃል፡ በማንተም አትዝጋው! ዓመፀኛው፡ ወደፊት ያምፅ! ርኩሱም፡ ወደፊት ይርከስ! ጻድቁም፡ ወደፊት፡ ጽድቅ ያድርግ! ቅዱሱም፡ ወደፊት፡ ይቀደስ!' አለኝ። 'እነሆ፡ በቶሎ እመጣለሁ፡ ለእያንዳንዱም፡ እንደሥራው መጠን እከፍል ዘንድ፡ ዋጋዬ፡ ከእኔ ጋር አለ!'"*[፻፲፩] ሲል በጻፈው መልእክት አረጋግጦታል።

**የምጽአቱ፡ ምልክቶቹ እንጂ፡ ቀኑ፡ በትውልዱ ዘንድ ስለአለመታወቁ።**

**ጥያቄ፦** *"ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት፡ ግን፡ ከአባት ብቻ በቀር፡ የሰማይ መላእክትም ቢኾኑ፡ ልጅም ቢኾን፡ የሚያውቅ የለም።" ተብሎ የተጠቀሰው ቃል፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ ኢየሱስ ክርስቶስም ቢኾን፡ የመምጫውንና የዓለሙን ፍጻሜ፡ ቀኒቱንና ሰዓቲቱን አያውቅም ማለቱ ነውን?*

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

መልስ:- ይህ ቃል፡ በዚህ መልክ የቀረበው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ይህን ምሥጢር፡ የሚያውቀው፡ ከአባቱ ጋር አንድ በኾነበት፡ በእግዚአብሔርነቱ ባሕርይ እንጂ፡ በሰውነቱ አለመኾኑን ለማሳየት እንደኾነ፡ ለእውነተኛ ሃይማኖታዊ ሰው ግልጽ ነው። ደቀ መዛሙርቱ ላቀረቡለት ጥያቄያቸው፡ ጌታ፡ እንዲህ አድርጎ ሳይመልስላቸው ቀርቶማ ቢኾን ኖሮ፡ የመምጣቱና የዓለሙ ፍጻሜ፡ መቼ እንደሚኾን፡ ምሥጢሩን ይገልጽላቸው ዘንድ፡ ደቀ መዛሙርቱ ጠይቀውት፡ በሚነግራቸው ጊዜ፡ "ይህን ያህል፡ ዘርዝረህ ከነገርኸን፡ እንግዲያው፡ ቀኒቱንና ሰዓቲቱንም፡ ለይተህና ጨምረህ አስታውቀን!" ብለው፡ አስጨንቀው በያዙትና ባስቸገሩት ነበር። .

እርሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ አብሩዋቸው ሳለ፡ ራሱን፡ ለእነርሱ፡ ለደቀ መዛሙርቱ ያሳወቀው፡ "የሰው ልጅ" እያለ፡ መላልሶ በመጥራት ነበረ፡ እነርሱም፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ወደፊት፡ ምሥጢራቱን ኹሉ፡ በጊዜው ገላልጾ እስኪያሳውቃቸው ድረስ፡ ሃይማኖታቸው ይገኝ የነበረው፡ ገና በ"ወጣኒነት" ደረጃ ነበር። ከዚህ የተነሣም፡ ከእርሱ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ኹሉ፡ በይበልጥ፡ ከሰውኛው የአስተሳሰብ መጠን ያላለፈ ነበረ፡ ስለዚህ፡ ለጥያቄያቸው መልስ ይኾናቸው ዘንድ፡ "ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት፡ ከአባቱ፡ ከእግዚአብሔር አብ በቀር፡ እኔ ልጁም እንኳ ብኾን፡ (በሰውነቱ) ላውቅ አልችልም!" በማለት፡ ነገሩን፡ ባጭር በዘጋባቸው ጊዜ፡ ነገሩን ከመቀበል በቀር፡ ሌላ ቀጣይ ጥያቄን አንሥተው ለመጠየቅ አስፈላጊ ኾኖ አላገኙትም፡ እንደዚያማ ባይኾን ኖሮ፡ በእግዚአብሔር ልጅነቱ ተጠራጥረው፡ "ይህ፡ እንዴት ሊኾን ይችላል" ብለው፡ እንደገና ሳይጠይቁት ባልቀሩ ነበር፡ ወይም፡ ከእነርሱ መካከል፡ በየጊዜው እንዳደረጉት፡ ወደኋላቸው ተመልሰው በተለዩት ነበር።

ደቀ መዛሙርቱ፡ በሃይማኖታቸው ደረጃ፡ ከፍጹሙ ብቅዓት በደረሱ ጊዜማ፡ የእግዚአብሔርን፡ ያለፈና የዛሬውን፡ የመጪውንም ምሥጢራት ኹሉ፡ የማወቁ ኃይል ስለተሰጣቸው፡ ጥያቄውን፡ እንደገና ማቅረብም፡ መልስ መጠበቅም ሳያስፈልጋቸው ቀርቷል፡ ይህንም እውነታ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ፡ ባረገበት ቀን፡ "*'ጌታ ሆይ! በዚህ ወራት፡ ለእስራኤል፡ መንግሥትን ትመልሳለህን?' ብለው በጠየቁት ጊዜ፡ 'አብ፡ በገዛ ሥልጣኑ፡ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ፡ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፡ ነገር ግን፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ፡ ኃይልን ትቀበላላችሁ፡ በኢየሩሳሌምም፡ በይሁዳም ኹሉ፡ በሰማርያም፡ እስከምድር ዳርም ድረስ፡ ምስክሮቼ ትኾናላችሁ!' አለ።*" የሚለው[፲፪] የወንጌላዊው ቃል አረጋግጦታል።

ከዚህ ቃል የምንረዳው፡ ትልቁ ቍም ነገር፡ ከቶ ምንድር ነው? ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሊነግራቸው ያልፈለገውን፡ እነርሱም፡ ሊረዱት ይቻላቸው ያልነበረውን፡ የመምጫውንና የዓለሙን መጨረሻ፡ ትክክለኛ ቀንና ሰዓት የማወቁን ምሥጢር፡ ሊደርሱበት የሚቻላቸው፡ በሰውነታቸው የአእምሮ ኃይል ሳይኾን፡ በመንፈስ ቅዱስ ብቻ መኾኑን ነው።

## ምዕራፍ ፫፡ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት::

### ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን::

### የምጽአቱ፡ ምልክቶቹ እንጂ፡ ቀኑ፡ በትውልዱ ዘንድ ስለአለመታወቁ::

---

**ጥያቄ:-** *"ይህ ኹሉ እስኪኾን ድረስ፡ ይህ ትውልድ አያልፍም!" ያለው የትኛውን ትውልድ ነው?*

**መልስ:-** ከአዳምና ሔዋን አንሥቶ፡ እስከኖኅ ዘመን፡ ሲወርድ ሲዋረድ የኖረው ትውልድ፡ በኖኅ መርከብ ከዳኑት በቀር፡ በጥፋት ውኃ ስለተደመሰሰ፡ "በንስሓ አልመለስም!" ብሎ፡ የተደመሰሰው፡ ያ፡ ኃጢአተኛ ትውልድ፡ "አንድ ትውልድ" ተብሎ፡ የመጀመሪያው ነው:: ኹለተኛው ትውልድ ደግሞ፡ በኖኅና በልጆቹ፡ እንደገና አቆጥቁጦ፡ በኹለት ዘርፍ የወረደው ነው::

ይህም፡ በአንድ በኩል፡ በሦስት ቅርንጫፎች ተከፋፍሎ፡ በተለየየ ዘር የቀጠለውና በንስሓ ባለመመለሱ፡ በመጨረሻው ትንሣኤ፡ በእሳት የሚደመሰሰው፡ የሴም፡ የካምና የያፌት ትውልድ ነው፡ በሌላ በኩል ደግሞ፡ በመልከ ጼዴቅ ግንድነት፡ ከእነዚህ ሦስት ቅርንጫፎች፡ በአንድነት ተዋሕዶ የቀጠለውና *ንግሥተ አዜብ (ኢትዮጵያ፡ እርሷም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በቅዱሱ ኪዳን ልጆቿ አማካይነት) በፍርድ ቀን፡ በክህደቱ፡ በዓመፁና በአመንዝራነቱ ኃጢአት፡ ከሚደመሰሰው ትውልድ ጋር ተነሥታ፡ ትፋረደዋለች፡ ታሳፍረዋለችም፡ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት፡ ከምድር ዳር መጥታለችና፡ እነሆም፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ::"* ተብሎ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረለት፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱና ምግባሩ ምክንያት፡ ከመጨረሻው ጥፋት የሚድነው፡ ኢትዮጵያዊው ትውልድ ነው:: *"ከሰሎሞን የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ!"* የተባለውም፡ ራሱ፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ" መኾኑን፡ እንደተገነዘባችሁት[፻፲፫] አምናለሁ::

**ጥያቄ:-** *የአምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን፡ የዳግም ምጽአቱንና የዓለሙን መጨረሻ በሚመለከት፡ ቀደም ብለህ፡ በሰፊው የዘረዘርካቸው፡ እነዚያ ኹሉ ምልክቶች፡ ዛሬ፡ ደርሰው እየታዩ ይመስልሃልወይ?*

**መልስ:-** ይህን ጥያቄማ፡ ለእኔ ልታቀርቡ አያስፈልጋችሁም፡ ለየራሳችሁ አቅርቡቻችሁ፡ መልሱን ልትሰጡ የሚገባችሁ፡ እናንተው እየራሳችሁ ናችሁ:: በአኹኑ ጊዜ፡ ምልክቶቹ ኹሉ፡ አንድ በአንድ፡ በሙሉ ደርሰው፡ ይኸው ታይዋቸው የለምን? ለዚህ እውነታም፡ ከእኔ ቀጥሎ፡ ኹለተኛውና ሦስተኛው ምስክሮች፡ እናንተው አይደላችሁምን? መኾናችሁ እኮ ነው!

**ጥያቄ:-** *ታዲያ፡ ምን ማድረግ አለብን?*

**መልስ:-** ከዚህ ኹሉ ውይይት በኋላ፡ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ፡ አኹንም፡ እኔኑ ነው የምትጠይቁኝ? ከጠየቃችሁኝማ፡ የምሰጣችሁ መልስ፡ አጭርና ቀጥተኛ፡ ግልጽም ነው::

## ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ይኸውም፡ *"ምንም ምክንያት ሳትፈጥሩና ሳታመሳውሉ፥ አንዳችም ቀጠሮ ሳትሰጡ፡ ሰው ኾኖ፡ በቤዛነቱ ባዳነን፡ ፈጣሪና በቅድስት እናቱ መንበር ፊት ቆማችሁ በምትፈጽሙት የቃል ኪዳን ምስክርነታችሁ በምታጸድቁት፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ፈጥናችሁ፡ በንስሓ እንጽታችሁ፡ የኢየሱስ ክርስቶስን፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መቀበል ብቻ ነው!"* የሚል ነው፤ እንዲህ ሊኾን እንደሚገባ፡ እናንተም፡ የምትስቱት አይመስለኝም።

**ጥያቄ፦** *እሺ! ይህንማ፡ ያለማመንታትና ያለመዘግየት እንፈጽማለን! ነገር ግን፡ ለዚህ እውቀትና ጸጋ በመብቃታችን፡ በምን ቃል ነው እግዚአብሔርን የምናመሰግነው? ለአንተስ እንዴት ነው ውለታህን የምንከፍለው?*

**መልስ፦** ለእግዚአብሔር ስለምታቀርቡት ምስጋናም ኾነ፡ ለእኔ ስለምትመልሱት ውለታ ልንገራችሁ! ወደእኔ መጥታችሁ፡ እንድንገናኝና ይህን ውይይት እንድናካኺድ፡ ገና በመጀመሪያ፡ ልቦናችሁን በማነሣሣታችሁ፥ ውይይቱንም፡ እስከዚህም ድረስ በትዕግሥት ጸንታችሁ ለመቆየት፡ ፈቃደኞች በመኾናችሁ፡ ፈጣሪያችን፡ ለፍጡሩ ኹሉ ያለውን ፈቃድና የሚያስደስተውን ምግባር ስለፈጸማችሁ፡ ኹለታችሁም፡ በኹለንተናችሁ፡ በሚሰማችሁ፡ በየራሳችሁ ደስታ ነው፡ እግዚአብሔር፡ ደስ ብሎት፡ ያን ደስታችሁን፡ የምስጋና ቊርባን አድርጎ የተቀበለላችሁ። እኔም፡ እንደታናሽነቴ፡ በዚያ ደስታ ተመልቼ ነው፡ ይህን ምሥራች የምነግራችሁ።

ይህንም፡ ታላቁ መምህራችንና መድኃኒታችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"ንስሓ ከማያስፈልጋቸው፡ ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ፡ ንስሓ በሚገባ፡ በአንድ ኃጢኣተኛ፡ በሰማይ፥ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት፡ ደስታ ይኾናል!"* ባለው ቃሉ አረጋግጦታል። ይህ ቃሉ፡ በእናንተ ላይ[፻፲፱] ተፈጽሞ በማየቴ፡ እኔም፡ ትንሹ አገልጋዩ፡ ውለታዬን ተከፍያለሁና አታስቡ!

ፈጣሪያችሁ፡ ስላደረገላችሁ ስለዚህ ኹሉ ቸርነቱ፡ ለእርሱና ለቅድስት እናቱ፡ የምታቀርቡላቸው የምስጋናና የሰላምታ ቃላት አሉላችሁ፤ እነርሱንም፡ ወደፊት በምንደርስበት፡ በጸሎቱ ክፍል ውይይታችን ውስጥ፡ "ኢትዮጵያውያን፡ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት የምስጋና ጸሎት" እና "ኢትዮጵያውያን ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት የሰላምታ ጸሎት" በሚል አርእስት ስለምናነሳቸው፡ በዚያን ጊዜ ትሰሟቸዋላችሁ።

**ጥያቄ፦** *እንግዴህ፡ ምን እናደርጋለን? እስከዚያው፡ ፈጣሪያችንን፡ ከነእናቱ፡ "ተመስገን!"፥ ለአንተም፡ "እግዚአብሔር ይስጥልን!" ማለት ብቻ ነዋ!*

**መልስ፦** አዎን! ሊባል የሚገባው፡ ይኼው ብቻ ነው።

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን።

### የምጽአቱ፡ ምልክቶቹ እንጂ፡ ቀኑ፡ በትውልዱ ዘንድ ስለአለመታወቁ።

---

ጥያቄ፡- *የመጨረሻው የምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ሐተታ፡ በዚህ አበቃ ማለት ነው?*

መልስ፡- አዎን! ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ብቻ ሳይኾን፡ አምስቱም፡ አዕማደ ሃይማኖት፡ በዚህ ተጠቃልለው ያበቃሉ።

### ከክርስትና ውጭ ስለኾኑት፡ ስለሌሎቹ ሃይማኖቶች።

ጥያቄ፡- *በተለይ ሃይማኖትን በሚመለከት፡ የምናደርገውን ውይይት ከመዝጋታችን በፊት፡ አንድ አጠቃላይ ጥያቄን እንድናቀርብልህ ፍቀድልን! ይህም፡ በምድር ላይ፡ ከክርስትና እምነት ውጪ የኾኑ፡ ልዩ ልዩ ሃይማኖቶችን የሚመለከት ነው።*

*በዚህ ረገድ፡ በቅርብ ምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉት፡ የይሁድናና የእስልምና ሃይማኖቶች ናቸው። ራቅ ሲልም፡ በአረማዊነት እና/ወይም በአሕዛብነት የሚፈረጁትን፡ በሕንድ፡ በቻይና፡ በጃፓንና በቀሩት የሩቅ ምሥራቅ አገሮች የሚኖሩትን፡ ቡዲስቶችንና ኮንፉሺዮኖችን፡ እንዲሁም፡ መናፍስትና ጣዖት አምላኪዎችን፡ አዲሳን ሃይማኖተኞችን፡ ደግሞም፡ ሃይማኖትና እግዜር አልባዎችን የመሰሉት ሰብአውያን ፍጡሮች፡ ሊጠቀሱ ይቻላል። ታዲያ! እዚህ ላይ፡ ጥያቄያችን፡ "እነዚህ ኹሉ፡ በመጨረሻው የእግዚአብሔር ፍርድ ጊዜ፡ እንዴት ሊኾኑ ነው? ይድናሉ? ወይስ አይድኑም?" የሚል ነው።*

መልስ፡- "መዳን" ማለት ምንድር ይመስላችኋል? እግዚአብሔር፡ ሰው በኾነው፡ በአንድ ልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕትነትና ቤዛነት፡ መላውን ፍጥረቱን፡ ከራሱ ጋር አስታርቆ፡ በዚህ መድኃኒትነቱ፡ "መድኃኔ ዓለም" ተብሎ፡ የመዳንን ዘውድ፡ ለአንደኛውና ለመጨረሻው ጊዜ፡ ለሰው ልጆች ኹሉ ያቀዳጀ መኾኑን **ማወቅ** እኮ ነው። አንድ ሰው፡ ይህን እውነታ፡ በእርግጥ ያወቀ እንደኾነ፡ ባላየውና በማያውቀው፥ ወደፊት፡ ከሞተ ሥጋ በኋላ፡ "ለዘለዓለም እኖርበታለሁ!" ብሎ፡ በሚያስበው መልካም ዓለም ለመኖር፡ በተስፋ እየተጠባበቀ መቈየት ሳይኾን፡ ዛሬ፡ በሕይወተ ሥጋ እያለ፡ በእውን በሚመላለስበት ምድር ላይ፡ በሥጋውም፡ በነፍሱም፡ በመንፈሱም፡ ፍጹም ጤናማና ሰላማዊ የኾነ የሕይወት ጣዕምን እያጣጣመና በተድላ ገነት ረክቶ በፍጹም ደስታ መኖር ማለት እኮ ነው።

ይህ፡ የመዳን ጽዋ፡ ለእያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ ከፈጣሪው፡ በነፍስ ወከፍ፡ በየእጁ፡ ተሰጥቶት ይገኛል። ከዚህ በኋላ፡ ምርጫው፡ የእርሱ ፋንታ ነው፥ ለመዳን የሚፈልግ፡ ይድናል፥ ለመጥፋት የሚፈልግም፡ ይጠፋል፥ ማለትም፡ መዳኑም፥ መጥፋቱም፡ ከራሱ ምርጫ የተነሣ ነው። በዚህ ረገድ ያለው፡ የእግዚአብሔር ፍርድ፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ ተሰጥቶ አብቅቷል፥ እንግዲህ ወዲህ፥ ወይም፡ ከአዲሱ ኪዳን በኋላ፡ ሌላ የሚጠበቅ ፍርድ የለም።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ፍርዱም፡ በከሳሽና በተከሳሽ መካከል በተደረገ የችሎት ክርክር ላይ፡ ፡ተሰጠ የጻኝነት ብያኔ፡ "ይግባኝ!" የሚያስፈልገው አይደለም፡ ንያቱም፡ ራሱ በፈጠረው ፍጡሩ፡ የክህደትና የዓመፅ በደል የተፈጸመበት፡ አድራጊው ፈጣሪ፡ ፍጡሩን፡ በመልኩ ፈጥሮ፡ የሾመና የሸለመ ሲኾን፡ ፡ ተበድሎና ተንቆ፡ እንደገና፡ ያን በደሉንና ጥቃቱን፡ ራሱ፡ በእውነተኛው ፡ተ፡ ካየ በኋላ፡ በበዳዩና በወንጀለኛው ፍጡሩ ላይ የተፈረደውን፡ ገሞትበቃ የደረሰውን ትክክለኛ ቅጣት፡ ራሱን፡ ለበዳዩ ቤዛ አድርጎ፡ ሥዋዕትነት በማቅረብ፡ ራሱ በፈቃዱ ስለተቀበለለት ነው፡፡

አዎን፡ ይህ ጻኝነት፡ "ይግባኝ" የሚያስፈልገው ብያኔ አይደለም፡፡ ዚህ፡ በግእዝ፡ 'ብሥራት'፡ በኢትዮጵያኛ፡ 'ምሥራች'፡ በግሪክኛም፡ ንጌል' የተባለውን፡ ይህን፡ የአዋጅ ቃል የሰማ ኹሉ፡ የሚሰጠው ምላሽ፡ ሺ!" የሚል ከኾነ፡ ይድናል፡ "እምቢ!" የሚል ከኾነም፡ ይጠፋል፡ ምርጫው ርሱ፡ የሰብአዊው ፍጡር መኾኑ፡ በዚህ ሥርዓት፡ ግልጽ ኾኖ ይታያል፡፡

ፈጣሪ፡ ፍጡሩን ለማዳን የፈጸመውን፡ ይህን፡ የቸርነት ሥራ፡ ወንጌላዊው፡ እንዲህ ሲል በጻፈው ቃል፡ አጠቃልሎ ገልጾታል፡፡ *"የመነበት ኹሉ፡ ለዘለዓለም ሕያው ኾኖ እንዲኖር እንጂ እንዳይጠፋ፡ እግዚአብሔር፡* ነንድ ልጁን [ኢየሱስ ክርስቶስን]፡ *ቤዛ አድርጎ፡ አሳልፎ እስኪሰጥለት ድረስ፡ ዓለሙን እንዲህ ወድዶታልና፡፡ የመነበት ኹሉ እንዳይጠፋ፡ የዘለዓለም ሕይወትንም እንዲያገኝ እንጂ፡፡ እግዚአብሔር፡ በእርሱ፡ ዓለሙን፡ ሊያድን እንጂ፡ በዓለሙ ላይ ሊፈርድበት፡ ልጁን፡ ወደዚህ ዓለም አልላከውምና፡፡ በእርሱ የመነ፡ አይፈረድበትም፡ በእርሱ ያላመነ ግን፡ ፈጽሞ ይፈረድበታል፡*[፻፲፯] *በአንዱ፡ በእግዚአብሔር ልጅ ስም አላመነምና፡፡"*

ምናልባት፡ ይህን፡ የምሥራቹን የአዋጅ ቃል ያልሰማ ቢኖር ግን፡ የሚድነው፡ ወይም የሚጠፋው፡ በራሱ ሕሊና፡ በከበበው ሥነ ፍጥረትና በሚነግሩት እውነተኞች ምሁራንና ቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት፡ እግዚአብሔርን ለማወቅ፡ ባደረገው ጥረትና ባሳየው ፈቃደኛነት መጠን ይኾናል፤ ይህንም፡ ሓዋርያው፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመልቶ፡ ለአረማውያንና ለአሕዛብ የተናገራቸው፡ እንዲህ የሚሉት ቃሎቹ ያስረዳሉ፡-

*"እናንተ ሰዎች! ...ከዚህ ከንቱ ነገር፡ ሰማይንና ምድርን፡ ባሕርንም፥ በእነርሱም ያለውን ኹሉ ወደፈጠረው ሕያው እግዚአብሔር፡ ዘወር ትሉ ዘንድ፡ ምሥራቹን እንሰብካለን፡፡ እርሱ፡ ባለፉት ትውልዶች፡ አሕዛብን ኹሉ፡ በገዛ ራሳቸው ጐዳና ይኼዱ ዘንድ ተዋቸው፡፡ ከዚህም ኹሉ ጋር፡ መልካም ሥራን እየሠራ፡ ከሰማይ ዝናብን፡ ፍሬ የሚኾንበትንም ወራት ሲሰጠን፥ ልባችንንም፡ በመብልና በደስታ ሲሞላው፡ ራሱን፡ ያለምስክር አልተወም፡፡*

*"የአቴና ሰዎች ሆይ! እናንተ፡ በኹሉ ነገር፡ አማልክትን፡ እጅግ እንደምትፈሩ እመለከታለሁ፡፡ የምታመልኩትን እየተመለከትሁ ሳልፍ፡ 'ለማይታወቅ አምላክ' የሚል ጽሕፈት ያለበትን መሠዊያ ደግሞ አግኝቻለሁና፡፡*

# ምዕራፍ ፫፤ አምስቱ አዕማደ ሃይማኖት።

## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን።

### ከክርስትና ውጭ ስለኾኑት፡ ስለሌሎቹ ሃይማኖቶች።

---

*"እንግዲህ፡ ይህን፡ ሳታውቁ የምታመልኩትን፡ እኔ እነግራችኋለሁ፦ ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ኹሉ የፈጠረ አምላክ፡ እርሱ፡ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና፡ እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም፡ እርሱም፡ ሕይወትንና እስትንፋስን፡ ኹሉንም፡ ለኹሉ ይሰጣልና፡ አንዳች እንደሚጐድለው፡ በሰው እጅ አይገለገልም። ምናልባትም፡ እየመረመሩ ያገኙት እንደኾነ፡ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ፡ በምድር ኹሉ ላይ እንዲኖሩ፡ የሰውን ወገኖች ኹሉ፡ ከአንድ ፈጠረ፡ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ሥፍራ፡ ዳርቻ መደበላቸው። ቢኾንም፡ ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም። ከእናንተ፡ ከባለቅኔዎች፡ አንዳንዶች፡ 'እኛ ደግሞ፡ ዘመዶቹ ነንና!' ብለው እንደተናገሩ፡ በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን፡ እንኖርማለን። እንግዲህ፡ የእግዚአብሔር ዘመዶች ከኾን፡ አምላክ፡ በሰው ብልሃትና አሳብ፡ የተቀረፀውን ወርቅ፡ ወይም፡ ብር፡ ወይም፡ ድንጋይ እንዲመስል እናስብ ዘንድ አይገባንም። እንግዲህ፡ እግዚአብሔር፡ ያለማወቅን ወራት አሳልፎ፡ አኹን፡ በየቦታቸው፡ ንስሓ ይገቡ ዘንድ፡ ሰውን ኹሉ ያዝዛል፡ ቀን ቀጥሮአልና፡ በዚያም ቀን፡ ባዘጋጀው ሰው እጅ፡ በዓለሙ ላይ፡ በጽድቅ ሊፈርድ አለው። ስለዚህም፡ እርሱን፡ ከሙታን በማስነሣቱ፡ ኹሉን አረጋግጧል።"*

ደግሞም፡ ሌላው፡ ከዚህ ጋር ሊጠቀስ የሚገባው ቃሉ፡ እንዲህ ይላል፦ *"እግዚአብሔር፡ ለሰው ፊት አያደላምና። ያለሕግ (ያለሕገ ኦሪት፡ ማለትም፡ እግዚአብሔርን ሳያውቁ፡) ኃጢአት ያደረጉ ኹሉ፡ ያለሕግ ደግሞ ይጠፋሉና፡ ሕግም ሳላቸው፡ ኃጢአት ያደረጉ ኹሉ፡ በሕግ ይፈረድባቸዋል፡ በእግዚአብሔር ፊት፡ ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ፡ ሕግን የሚሰሙ፡ ጻድቃን አይደሉምና። ሕግ (ሕገ ኦሪት) የሌላቸው አሕዛብ፡ ከባሕርያቸው፡ የሕግን ሥርዓት ሠርተው፡ በሕግ ይመራሉ፤ እነርሱ፡ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ፡ ለራሳቸው፡ ሕግ ናቸውና፡ ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፡ አሳባቸውም እርስ በርሱ ሲካሰስ፡ ወይም ሲያመካኝ፡ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ፡ በምግባራቸው፡ ግልጽ አድርገው ያሳያሉ።"* ፻፲፮

ይህ፡ የሐዋርያው ቃል፡ ጸንቶ የቆየው፡ ራሱ፡ ሐዋርያው እስከነበረበት ጊዜና ስብከቱ እየተስፋፋ እስከኼደባቸው ተከታታዮቹ ዘመናት ድረስ መኾኑን አስተውሉት! ይህም ማለት፡ መልእክቱ፡ አኹን ባለንበት፡ በዚህ ዘመን፡ ያበቃ መኾኑ፡ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአትና ለዓለሙ መጨረሻ፡ ምልክት የኾነው፡ *"ለአሕዛብ ኹሉ፡ ምስክር እንዲኾን፡ ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት ምሥራች (ወንጌል)፡ በዓለሙ ኹሉ ይሰበካል!"* የሚለው የጌታ ትንቢታዊ ቃል በመፈጸሙ ይረጋገጣል። ለዚህ እውነታም፡ ክርስቲያኖችና የእግዚአብሔር አማኞች ብቻ ሳይኾኑ፡ አረማውያንና አሕዛብ ጭምር፡ ምስክሮች ናቸው፤ ይኸውም፡ ምሥራቹ፡ በዓለም ኹሉ ቋንቋዎች ተተርጕሞና ተጽፎ፥ ሐዋርያቱና መምህራኑም፡ በመላዋ ምድር ላይ ተበትነው፡ መልእክቱን፡ በአካል እያሰሙ ያዳረሱት ከመኾናቸው ጋር፡ በነፋስ ድምፅና በነፋስ ሥዕል፡ በኀዋው አውታርና በሌላውም የመገናኛ ዘዴ ሳይቀር ተስፋፍቶ መሠራጨቱ፡ እነሆ፡ በገሃድ ስለሚታይ ነው።

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

---

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዚያ የባሕርይ ክብሩ፡ ዛሬ፡ ቢመጣ፡ በመላው ዓለም፡ በምድር፥ በባሕርና በደሴታት ላይ፥ ምናልባትም፡ በውቅያኖሱ ጥልቀትና በጠፈሩ ምጥቀት ውስጥ ከሚገኙ ሰብአውያን ፍጡሮች መካከል፡ "በእርሱ ስለተገለጠችው፡ ስለእግዚአብሔር መንግሥትና ስለመዳን ያስተላለፈውን፡ የምሥራቹን ዜና፡ 'አልሰማሁም!' ሊል የሚችል፡ ሥጋ ለባሽ ግለሰብ ይኖራል!" ብሎ ማሰቡ እንኳ ያዳግታል። እንግዲህ፡ የምሥራቹ ቃል የተሰበከው፡ እንዲህ፡ *ለኹሉ፡ እንደየሃይማኖታዊ ሥራው የሚከፍለው ዳኛ* በገሃድ ተገልጾ በሚመጣበት ጊዜ፡ ስለመዳን፡ ከፈጣሪ የተላለፈውን ምሥራች፡ "መቼ ሰማሁ?" የሚለውን፡ የአሕዛብን ምክንያት፡ ለመሻር መኾኑ ሊታበል አይቻልም።

ስለዚህ፡ በምድር ላይ የሚኖሩት፡ ልዩ ልዩ ሃይማኖት ያላቸውና የሌላቸው ሰብአውያን ፍጡሮች ኹሉ፡ የምሥራቹን መልእክት ሰምተውና ተቀብለው፡ ለመዳን ወይም ላለመዳን፡ ምርጫው የእነርሱ ነው። ምናልባት ያልሰሙ ቢኖሩ፡ መዳናቸው ወይም መጥፋታቸው የሚወሰነው፡ ለሰው ልጆች በተደረገው መለኮታዊ ትድግና የተዋጀው፡ የየሕሊናቸው ሕግ በሚፈርድባቸው መሠረት እንደሚኾን፡ ቀደም ብሎ ከተጠቀሰው፡ ከሐዋርያው ቃል ጋር፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን፡ በትሩፋቱ ያመለክተናል።

\+ \+ \+

# ምዕራፍ ፬፤

## ሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ሥርዓቶች::

*ጥያቄ:- እኛ ኢትዮጵያውያን: በቅዱሱ ኪዳን: ከእግዚአብሔር የተቀበልናት ሃይማኖታችን: በተለይ: በእኛ ዘንድ: ስትገለጽ የኖረችባቸውን: ፩ኛ: "የኢትዮጵያውያን": ፪ኛ: "የሐዋርያት": ፫ኛ: "የሠለስቱ ምዕት" የሚባሉትን: ሦስቱን የሃይማኖት ጸሎቶች: እንዲሁም: አምስቱ "አዕማደ ሃይማኖት" ወይም "የሃይማኖት ምሰሶዎች" የተባሉትን: እነዚህን እጅግ የመጠቁና የጠለቁ ምሥጢራት: አውቀንና ተቀብለን ልናምንባቸው የምንችለው: በሥጋዊው ብቻ ሳይኾን: በይበልጥ: በመንፈሳዊው አእምሮአችን መኾኑን አስረድተኸን: እኛም: ይህንኑ: የእግዚአብሔር መመሪያ: ፈልገንና ፈቅደን: ወድደንና መርጠን ስለተከተልን: ይኸው: እየራሳችንን: ለዚህ ዕድል ለማብቃት ችለናል::*

*እንግዲህ: ይህችን ሃይማኖታችንን: እንዲህ ባለ መልክና ኹኔታ: ኢየንዳንዳችን: በግል: ኹላችንም: በጋራ አውቀናትና አምነንባት ከተቀበልናት በኋላ: ሕይወት አድርገን ልንኖራት የምንችለው እንዴት እንደኾነ: ወይም: እንዴት ሊኾን እንደሚገባ: የተዘጋጀ አንዳች ሥርዓት ካለ: ብታመለክተን?*

መልስ:- ይህ ውይይት: አንድ ኢትዮጵያዊ: የእግዚአብሔር በኾነችው ሕይወት ሊኖር ስለሚችልበት ሥርዓት: አለዚያ ደግሞ: የዲያብሎስ ለኾነው: ለሞት ሊዳረግ ስለሚችልበት ጠንቅ: እውነቱን ተረድተን: ከመጨረሻው እውቀት እንደርስ ዘንድ: በከፍተኛ መሥዋዕትነት የምናካኺደው ገላ ስለኾነ: ውይይቱን: በጀመራችሁበት የቀኑም ነገር ይዘታችሁ: እንዲህ: በማስተዋል መመልከታችሁን እንደምትቀጥሉ ተስፋ አደርጋለሁ::

አዎን! እስካሁን ባገኛችሁት እውቀት: መጀመሪያ: ሰው ኹሉ: ለዚህ የመጨረሻ ዕድል ሊበቃ የሚችልበት ጸጋ: ከፈጣሪው: በቸርነት የተሰጠው መኾኑን፣ በእግዚአብሔር ፈቃድ ተወጥኖ: ለፍጹምነት የበቃው: ይህ: የህልውና ምዕራፍ የተገለጠባት ምሥጢርም: "ሃይማኖት" መኾኗን: ተገንዝባችኋል:: ከእግዚአብሔር ፈቃድ ሠርፃ: ይህን የመሰለውን ፍጹም እውቀት ያቀዳጀቻችሁን: ይህችን ሃይማኖት: ሕይወት አድርጋችሁ ትኖሩባት ዘንድ: ከእርሱ: ከፈጣሪያችሁ: በጸጋ ያገኛችኋት: ገና: ከሕፃንነታችሁ ጀምራችሁ መኾኑን: ቀደም ብለው: ተተንትነው በቀረቡላችሁ: በአም[illegible] አዕማደ ምሥጢራት አማካይነት ተረድታችኋል::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

እንግዲህ፡ ፈጣሪያችሁ፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ በተፈጥሮ ባሕርያችሁና በመንፈስ ቅዱስ ጣቶች፡ በየልባችሁ ጽላት ላይ ጽፏትና በየልቦናችሁ አሳድሮ፡ እንድትማርዋትና እንድታውቋት ያደረጋችሁን፡ እናንተም፡ ነፍስ አውቃችሁ፡ እየንዳንዳችሁ፡ ለዓቅመ አዳምና ለዓቅመ ሔዋን እስከደረሳችሁባት፡ እስከዚች ሰዓት ድረስ፡ ከእርሷ ሳትነዋወጹ የቆያችሁባትን፡ ይህችኑ ሃይማኖት ጠብቃችሁ፡ ለዚህ ውይይታችን አብቅታችኋታል። ከዚህ በኋላ፡ የሚቀጥለውና የሚጠበቀው፡ ለዚህ የሕይወት ማዕርግ ያበቃቻችሁን፡ እውነተኛዪቱን ሃይማኖት ካስገኘችላችሁ፡ ከዚች፡ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር፡ የእናንተም ፈቃድ የሠመረ እንዲኾን ነው። የሠመረ መኾኑ የሚታወቀውም፡ ይህችን፡ የእግዚአብሔር ሃይማኖት፡ በእናንተ በኩል፡ ወድዳችሁና ደስ ብሎአችሁ፡ በእውነተኛ ፈቃደኛነት ስታጸኗት፡ እርሷንም፡ በየግል ህልውናችሁና እናንተን ከመሰሉት ጋር በአንድነት፡ ሕይወት አድርጋችሁ መኖራችሁን፡ አጠናክራችሁ ስትቀጥሉባት ነው።

ይህች ሃይማኖት፡ ለእናንተና እናንተን ለመሰሉት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በነፍስ ወከፍ ተሰጥታ፡ ቀደም ብዬ በገለጽሁላችሁ መልክ፡ በየግላችሁ፡ በመሰሎች ወገኖቻችሁም መካከል ሰፍና፡ ከእነርሱ ጋር በአንድነት ለመኖር የሚያስችሏችሁን፡ የበረከትና የኀይል ጸጋዎችን የምታስገኝባቸው፡ የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች አሏት፡ እነዚህም፡ ቀደም ብዬ፡ ጠቅሼላችሁ እንደነበረው፡ "ሥርዓታተ ምሥጢራት፡ ዘቤተ ክርስቲያን" ይባላሉ፡ እነርሱም፡ ሰባት ናቸው።

*ጥያቄ:- ታዲያ፡ ስለእነዚህ፡ ሰባት የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች፡ እዚህ ላይ የምትሰጠን መግለጫ ምንድር ነው?*

*መልስ:-* የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችሁ፡ በምግባር ላይ ውላ፡ መለኮታዊዉን ጸጋና በረከት የምታስገኝባቸው፡ ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፡ የሚፈጸሙባቸው ሥርዓቶች፡ ሥርዓተ ጥምቀት፡ ሥርዓተ ቅዳሴ፡ ሥርዓተ ሜሮን፡ ሥርዓተ ክህነት፡ ሥርዓተ ተክሊል፡ ሥርዓተ ንስሓ፡ ሥርዓተ ቀንዲል ይባላሉ። የእነዚህንም ሥርዓታት ምሥጢርነት፡ ከዚህ አያይዤ፡ ለአኹኑ ጥያቄያችሁ ማስታገሻ ያህል፡ ለጊዜው፡ ባጭር ባጭሩ እገልጽላችኋለሁ፡ ከዚህ ውይይታችን የሚቀረው፡ የተሟላው ሐተታ ግን፡ በሚቀጥለው የመጨረሻ ውይይታችን ይብራራላችኋል።

፩ኛ፡ "ሥርዓተ ጥምቀት":- ካህኑ፡ በመጽሐፈ ክርስትና የታዘዘውን ጸሎት ካደረሰ በኋላ፡ ውኃውን፡ በትእምርተ መስቀል እየቀዘፈ፡ "አሐዱ አብ ቅዱስ፡ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፡ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ!" ብሎ በባረከው ጊዜ፡ ያ ውኃ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተለውጦ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዕለተ ዓርብ፡ በዕፀ መስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ፡ በጦር ከተወጋ ጎኑ፡ ለኀጢአት ሥርየት የፈሰሰውንና መለኮት የተዋሐደውን፡ ውኃና ደም ይኾናል።

# ምዕራፍ ፬፤
# ሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ሥርዓቶች::

፩ኛ: "ሥርዓተ ጥምቀት"፡- በዚ.ያ: "ማየ ገቦ": አንተ ወንዱ: በአርባ ቀንህ: አንቺ ሴቷ: በሰማንያ ቀንሽ: ተጠምቃችሁና ከኃጢአት ነጽታችሁ: የእግዚአብሔር ልጅ የኾናችሁበትን ጸጋ የተቀበላችሁበት ሥርዓት ነው:: የዚህን ሥርዓት ዝርዝር: በምሥጢረ ጥምቀት ሐተታ ውስጥ: በሚበቃ ተተንትኖ አግኝታችሁታል::

፪ኛ: "ሥርዓተ ቅዳሴ"፡- ካህኑ: ከንጹሕ ስንዴና ከጥሩ ወይን የተዘጋጁትን ኅብስትና ጭማቂ: በጸሕልና በጽዋ አድርጎ: በመንበረ ታቦቱ ላይ ካቀረበ በኋላ: "ዓለሙን ኹሉ የያዘ እግዚአብሔር አብ አምላካችን: ቡሩክ ነው፡ እኛን ለማዳን: ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ: የእግዚአብሔር አብ አንድ ልጁ: አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም: ቡሩክ ነው: ሕይወትን የሚሰጥ: ኹላችንንም የሚያነጻንና የሚያጸናን መንፈስ ቅዱስም ቡሩክ ነው" ከሚለው ጀምሮ: "በእውነት አምነው: ከእርሱ ለሚቀበሉ: ሕይወትና መድኃኒት: የኃጢአት ማስተሥረያም ሊኾን የሚሰጥ: የአምላካችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ: ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ: ይህ ነው!" እስከሚለው የእማሬ (የአመልካች) ጸሎት ድረስ: ኅብስቱንና ወይኑን: ባርኮና ቀድሶ: መለኮት የተዋሐደው ቅዱስ ቊርባን እንዲኾን የሚለውጥበት ሥርዓት ነው:: የዚህን ሥርዓት ዝርዝር: በምሥጢረ ቊርባን ሐተታ ውስጥ: በሚበቃ ተተንትኖ አግኝታችሁታል::

፫ኛ: "ሥርዓተ ሜሮን"፡- በሕፃንነታችሁ: ሥርዓተ ጥምቀት ከተፈጸመላችሁ በኋላ: በዚ.ያ: የክርስትና ልደታችሁ ጊዜ: በመንፈስ ቅዱስ: ከእግዚአብሔር ያገኛችሁት ልጅነታችሁ: ለዘለዓለም የጸና መኾኑን ለማረጋገጥ: በዋስትናነት የተቀበላችሁትን የመጨረሻውን ማኅተም: ካህኑ: በየአካላችሁ ሕዋሳት ላይ: ቅዱሱን ቅብዓት: በቀኝ ጣቶቹ በመቀባት: የሚፈጽመው ሥርዓት ነው:: የዚህን ሥርዓት ዝርዝር: በምሥጢረ ጥምቀት ሐተታ ውስጥ: በሚበቃ ተተንትኖ አግኝታችሁታል::

፬ኛ: "ሥርዓተ ንስሓ"፡- እግዚአብሔር አምላካችን: ለሰው ልጆች ኃጢአት ማስተስረያ ይኾን ዘንድ: ፍጹም ቊርባንና የዘለዓለም መሥዋዕት አድርጎ: ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያሳረገውን: የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ከመቀበላችሁ በፊት: የምትፈጽሙት ምግባር ነው፡በእርሱም: በአንድ ወገን: "አቤቱ አምላኬ! እኔን በደለኛውን ደካማ ፍጡርህን: ኃጢአቴን ኹሉ: ይቅር በለኝ!" ብላችሁ: ለእውነተኛው ካህንና ሊቀ ካህናት: ለኢየሱስ ክርስቶስ: በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ ኾናችሁ: የምታውቁትንና የምታስታውሱትን ኃጢአታችሁንና በደላችሁን ኹሉ ትናዘዙበታላችሁ: በሌላው ወገን ደግሞ: በመምህረ ንስሓችሁ ምክር: ዓቅማችሁ በሚፈቅድላችሁ መጠን: የቀኖና ጾምና የምሕላ ጸሎት: የአምልኮ ስግደትና የትሩፋት ምጽዋት በማድረግ: ከቸሩ ፈጣሪያችሁ: ሥርየትን (ይቅርታን) ታገኙበታላችሁ:: የዚህን ሥርዓት ዝርዝር: በምሥጢረ ቊርባን ሐተታ ውስጥ: በሚበቃ ተተንትኖ አግኝታችሁታል::

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፤
## "ፈጣሪዬ" የምለው እግዚአብሔር፡ ማነው?

፭ኛ፡ "ምሥጢረ ክህነት"፦ ለዲቁና፡ ለቅስናና ለጵጵስና የክህነት አገልግሎት የተጠሩ ኢትዮጵያውያን፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ከመልከ ጼዴቅ በወረሱት በረከት፡ ለዚህ ተልእኮ የሚያበቃቸውን ጸጋ ተቀብለው የሚሠየሙበት ሥርዓት ነው።

፮ኛ፡ "ምሥጢረ ተክሊል"፦ በክርስትና ጥምቀት፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን ጸጋና ክብር ተቀዳጅተው፡ ንጽሕናቸውን፡ በድንግልና ጠብቀውና ራሳቸውን በንስሓ አድሰው የሚገኙ፡ ለዓቅመ አዳምና ለዓቅመ ሔዋን ያደረሱ፡ አንድ ኢትዮጵያዊ ወንድና አንዲት ኢትዮጵያዊት ሴት፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ነግሠውና ለዘለዓለም፡ ሕያዋን ኾነው የሚኖሩ መኾናቸው በይፋ ተገልጦ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ በወረሱት ጸጋና በረከት፡ የጋብቻቸው አንድነት የሚፈጸምበት ሥርዓት ነው።

፯ኛ፡ "ምሥጢረ ቀንዲል"፦ ከምእመናን ወገን፡ ከወንዶችም ኾነ ከሴቶች መካከል የታመመ ቢኖሩ፡ ከሕመማቸው ይፈወሱ ዘንድ፡ ጸሎት ተደርጎበት፡ የተዘጋጀውን ቅዱስ ቅብዓት፡ ከሀናቱ፡ ከጸሎት ጋር፡ ሕሙማኑን የሚቀቡበት ሥርዓት ነው።

እነዚህ፡ ሰባት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፡ እያንዳንዳቸው፡ በተናጠል ኾነ፡ ኹሉም በአንድነት፡ ካህናቱና ምእመናኑ በተገኙበት ተከናውነው ይፈጸማሉ፡ የሚፈጸሙባቸውም ዝርዝር ሥርዓቶችና ጸሎቶች አሏቸው። እነዚህም፡ ቀደም ብዬ እንዳመለከትኋችሁ፡ በሚቀጥለው የመጨረሻ ውይይታችን ጊዜ ይቀርቡላችኋል።

\+ \+ \+